# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 218 ሚያዝያ 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አባ ማትያስ


ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ


ፓስተር ጻዲቁ አብዶ


ቄስ ዶክተር ዮናስ

# ምዕመኑ የትንሳዔን በዓል

## የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብና በመርዳት ሊያከብረው እንደሚገባ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተሮች**

አዲስ አበባ፡- ምዕመኑ የትንሳዔን በዓል የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብና በመርዳት ሊያከብረው እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶች መልዕክት አስተላለፉ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አባ ማትያስ የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ባስተላለፉበት ወቅት እንደገለጹት፤ የፋሲካን በዓል ስናከብር የተራቡትን በመመገብ፣ የታረዙትን በማልበስ፣ የተጨነቁትን በማጽናናት፣ እንዲሁም የተገኘውን የሰላም ጭላንጭል ይበልጥ ለማስፋፋትና የሀገር አንድነቱን በዕርቅ ዘላቂ ለማድረግ ቃል በመግባት ሊሆን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ ለሁላችንም ከበቂም በላይ ናት ያሉት አባ ማትያስ ፤ የእኔ ነው በሚል ደካማ አመለካከት ራሳችንን በራሳችን አንጉዳ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የትንሳዔ በዓልን አስመልክተው ለመላው ምዕመናን ባስተላለፉት መልዕክት፤ ምዕመኑ የትንሳዔን በዓል በምስጋና፣ በውዳሴ፣ በፍቅርና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያሉ ወገኖችን በማሰብና በመርዳት ማክበር አለበት ብለዋል፡፡

የጥላቻ ንግግርን በትንሳዔው የምስራች በመለወጥ በዓሉን በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት ማክበር እንደሚገባ የጠቆሙት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ፤ ትንሳዔ ከሁሉም ነገድ፣ ከሁሉም ቋንቋ የተዋጀ ምስጢር ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም ምዕመናኑ በዓሉን ያለምንም መከፋፈልና መገለል ሲያከብር ነውና ትንሳዔ ተከበረ የሚባለው በትንሳዔው የሚገለል የሰው ልጅና ማኅበረሰብ ሊኖር አይገባም ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻድቁ አብዶ በዓሉን አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ፤ የክርስቶስን ምሳሌ ተከትለን ራሳችንን

ምዕመኑ የትንሳዔን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል






## መጽሐፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየር የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ ነው

ገጽ 11

# “የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ ምንም ጥርጥር የለውም ”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ሁሉ የሀገራችን ብልጽግና እውን እንደሚሆንና የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ ምንም ጥርጥር የለውም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የትንሳኤን በዓል በማስመልከት ትናንት ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንዳሉት፤ ሀገራችን የትንሣኤዋ ዋዜማ ላይ ነች። የምናያቸው ፈተናዎች የሕማማት ሰሞን ፈተናዎች ናቸው። እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ሁሉ የሀገራችን ብልጽግና እውን እንደሚሆን፣ የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ ምንም ጥርጥር የለውም።

በክርስቲያኖች ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ ተሰጥቷቸው ከሚከበሩ በዓላት መካከል በዓለ ትንሣኤው በቀዳሚነት ይጠቀሳል። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የፍቅር ጥግ የታየበት፣ የዕርቅና የይቅርታ ትርጉም የተገለጠበት፣ ምሕረትና ደኅንነት የተረጋገጠበት ታላቅ በዓል ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ፍጹም ፍቅር ከክብር ዙፋን ላይ

“የኢትዮጵያችን ትንሣኤ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# “የክልል ልዩ ኃይል የሚባል አደረጃጀት አይኖርም”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የክልል ልዩ ኃይል የሚባል አደረጃጀት አይኖርም ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የክልል ልዩ ኃይሎችን በፌዴራልና የክልል የጸጥታ ተቋማት መልሶ የማደራጀት ስራ የመከላከያ ጀነራሎች፣ የፌዴራል ፖሊስ እና የክልል የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት በተካሄደው የግምገማ መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ የክልል ልዩ ኃይሎች እንደገና በመደራጀታቸው ኅብረ ብሄራዊ ጠንካራ የጸጥታ ተቋም ይገነባል። ስለሆነም የክልል ልዩ ኃይል የሚባል አደረጃጀት የለም፤ አይኖርም፡፡

ኢትዮጵያ ከነበረችበት የጸጥታ ችግር በፍጥነት መውጣቷን የገለፁት ፊልድ ማርሻሉ፤ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በመልካም ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል። የክልል ልዩ ኃይሎች አደረጃጀት ህጋዊ አለመሆን፣ በክልሎች መካከል እንደ ስጋት መተያየት እንዲሁም ችግሮችን በኃይል ለመፍታት የሚደረገው



እንቅስቃሴ አደረጃጀቱን ለመቀየር አስገድዷል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በሁሉም ክልሎች መልሶ የማደራጀት ስራው ተጠናክሮ መቀጠሉን ጠቁመው "የክልል ልዩ

“የክልል ልዩ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



# የምገባ ማዕከላቱ በቀን ለ35 ሺህ ዜጎች ምግብ የማቅረብ አቅም ፈጥረዋል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ማዕከላት በቀን እስከ 35 ሺህ ዜጎች የመመገብ አቅም እንዳላቸው የምገባ ኤጀንሲው አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አንችነሽ ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ከሚከናወኑ ሰው ተኮር ተግባራት አንዱ የሆነው የምገባ አገልግሎቱ በ16 ማዕከላቱ በቀን እስከ 35 ሺህ ዜጎች የመመገብ አቅም አለው፡፡

ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ በብዛት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ያሉ ነዎሪዎች የሚገኙበት አካባቢዎችን በመለየት በቦሌ ክፍለ ከተማ ሁለት፣ በየካ ክፍለ ከተማ ሁለት፣ አራዳ ክፍለ ከተማ አንድ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ አራት፣ ልደታ ክፍለ ከተማ ሁለት፣ አቃቂ ክፍለ ከተማ አንድ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ሁለት እንዲሁም በሌሎች ክፍለ ከተሞች በአጠቃላይ አስራ ስድስት የምገባ ማዕከላት አሉ ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ አንችነሽ ገለጻ፤ የዚህ ምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ለዕለት ጉርስ ያጡ ተብለው በሴቶች፣ ህጻናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ስር የሚሰሩ ባለሙያዎች በየአካባቢው የሚለዩ ሲሆን፤ ቋሚ ተመጋቢዎች ኩፖን በመያዝ እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያት ከቤት መውጣት ለማይችሉ አቅመ ደካሞች ቤት ድረስ የሚሄድላቸው ሲሆን ለማንኛውም መጠቀም ለሚፈልግ ሰው ክፍት ነው፡፡

መስራት እየቻሉ ለተራቡት የስራ ስልጠና እና የህይወት ማሻሻያ ስልጠና በመስጠት እስከ ስድስት ወር ድረስ ብቻ በመቆየት ወደ መደበኛ ህይወት እንዲሸጋገሩ ይደረጋሉም ብለዋል፡፡

ማዕከሉ ለ557 ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፤ ከወረዳ እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በትስስር ከ10 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ስልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ የጠቀሱት ኃላፊዋ፤ ለምገባ የሚውለው ወጪ ሙሉ ለሙሉ በባለሀብቶች እና በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተሳትፎ የሚሸፈን እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

እንደተቋማቱ የሚሰሩት አገልግሎት ባህሪ እና የጊዜ አካሄድ ወጪያቸው የሚተመን መሆኑን ተናግረው፤ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የአቅርቦትና የሰራተኛ ወጪ በመሸፈን በዓመት 25 ሚሊዮን ብር በጀት በቀን እስከ ሦስት ሺህ ዜጎችን ለመመገብ እቅድ ይዞ እየሰራ እንደሆነ ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡

በተጨማሪም በግንባታ ዘርፍ ወጪ በመሸፈን የሚያግዙት ዳሽን ባንክ፣ አዋሽ ባንክ፣ ዘመን ባንክ፣ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የሚጠቀሱ መሆናቸውንና፤ የምግብ ግብአት በማሟላት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ሩሀ ሜዲካል ካምፓስ፣ ዲ.ኬ.ዲ ፋውንዴሽን እንዲሁም የተለያዩ የግል ባለሀብቶች እንደሚሳተፉ አብራርተዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት እና በተለያየ የስራ መስክ ላይ የሚሳተፉ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦችም እየደገፉ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ በአሜሪካ ግቢ የሚገኘው የተስፋ ብርሀን የምገባ ማእከል የምገባ አስተባባሪ የሆነችው ወ/ሮ ጋዲሴ ኡርባ በማእከሉ ከ2 ሺ 500 በላይ ተጠቃሚ ዜጎች መኖራቸውን ጠቅሳ፤ በቀን በአማካኝ ለ1 ሺ 450 ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል ብላለች፡፡ በተጨማሪም ለ38 ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል ስትል ገልጻለች፡፡

በዚህ ምገባ ማእከል ተጠቃሚ የሆኑት ወ/ሮ ትግስት ጸጋዬ በዚህ በተወደደ ኑሮ መንግስት ይሄንን እድል መስጠቱ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች እጅግ በጣም ጥሩ ስራ ነው ብለዋል፡፡

የሶስት ልጆች እናት የሆነችውና ሀይላንድ በመሸጥ ብቻዋን ልጆቿን የምታስዳድረው ወ/ሮ ትእግስት በበኩሏ፤ በአገልግሎቱ ኩፖን በመጠቀም ለእራሷ እና ለልጆቿ የእለት ጉርሷን እንደምታገኝ ገልጻለች፡፡ ለዚህም ካለው የስራ እጥረት እና የኑሮ ውድነት ለእራስዋ እና ለልጆቿ ትልቅ ሽክም እንዳቀላለት ተናግራለች፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ ጌጃ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው የምገባ ማእከል ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ለገሰ ግርማቸው እና ወ/ሮ እመቤት በቀለ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ መንግስት የጀመረው የምገባ ማዕከል አገልግሎት ከባዱን የኑሮ ሁኔታ እንዲቋቋሙ አስችሏቸዋል፡፡

# በእርድ ወቅት የእንስሳት ተረፈ ምርቶች አካባቢን እንዳይበክሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ህብረተሰቡ በበዓል ወቅት በሚከናወን እርድ የእንስሳት ተረፈ ምርቶች አካባቢን እንዳይበክሉ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ አሳሰበ፡፡



ዶክተር እሸቱ ለማ

የኤጀንሲው ዋና ዳሬክተር እሸቱ ለማ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኅብረተሰቡ በበዓላት ወቅት የእርድ ተረፈ ምርቶች የአካባቢውን ጽዳት እንዳያበላሹ ቆሻሻዎችን ለጽዳት ሰራተኞች መስጠትና ቆሻሻን በተገቢው መንገድ ማስወገድ ይጠበቅበታል።

ዶክተር እሸቱ እንደጠቆሙት፤ ኅብረተሰቡ ቆሻሻን መንገድ እና ቦይ ውስጥ ከመጣል ይልቅ ለጽዳት ሰራተኞች በሚመች መልኩ በማስቀመጥ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። በእርድ ወቅት የእንስሳት ተረፈ ምርቶች በአግባቡ ተለይተው ለጽዳት ሰራተኞች ካልቀረቡ በሚጣሉበት አካባቢ ላይ በመበስበስ ከፍተኛ የሆነ ሽታን ይፈጥራሉ። ይህም በኅብረተሰቡ ጤና ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ በእርድ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ከተቻለ ከተለያዩ በቆሻሻ ምክንያት ከሚከሰቱ ተላላፊ በሽታዎች እራስንና ቤተሰብንም መጠበቅ ይቻላል ብለዋል፡፡

ኤጀንሲው የትንሳኤና የኢድ አልፈጥር በዓላትን ታሳቢ ያደረጉ የንጽህና ሥራዎች ላይ ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በመስጠት ላይ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የእንስሳት እርድም ሆነ የዶሮ ተረፈ ምርቶች አካባቢን የመበከል ዕድላቸው ሰፊ ስለሆነ በየአካባቢው ትምህርት በመሰጠት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዶክተር እሸቱ እንደገለጹት፤ ቆሻሻ ከህብረተሰቡ፣ ከሆቴሎች፣ከቅብብሎሽ ጣቢያዎችና ከተቋማት የግል ጽዳት ድርጅቶች ይሰበሰባል። ቆሻሻን በተገቢው መንገድ የሚያስወግዱ ተቋማትና ማኅበራት በቂ ዝግጅት አድርገው መሳሪያዎችንና ግብአቶችን አሟልተው እንዲቀርቡ ጥረት ተደርጓል።

ኅብረተሰቡ እርድን በየመንደሩ ከማከናወን ይልቅ በቄራዎች በማድረግ ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ላይ ሊሳተፍ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኅብረተሰቡ ከዕርድ ተጨማሪ ተረፈ ምግብን ጨምሮ ሌሎች ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል ያሉት ዶክተር እሸቱ፤ ቆሻሻን መቅበርና ማቃጠል የራሱ የሆነ ችግር ያለው በመሆኑን ኅብረተሰቡ ከዚህ ድርጊት ተቆጥቦ ቆሻሻን ለይቶ ማስቀመጥ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

ኤጀንሲው በከተማ ደረጃ የሚቆጣጠራቸው 92 የጽዳት ማኅበራትና ከስምንት ሺህ በላይ አባላት መኖራቸውን ገልጸዋል።

# በጋምቤላ ከነዋሪዎች ጋር በቅንጅት በሚከናወኑ የጸጥታ ስራዎች ውጤት ተገኝቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከነዋሪዎች ጋር በቅንጅት በሚከናወኑ የጸጥታና የደህንነት ስራዎች ውጤት መገኘቱን የጋምቤላ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡



ቾንኮት ቾት

የጋምቤላ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቾንኮት ቾት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ነዋሪዎች ከጸጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት የክልሉን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ እያስጠበቁ ነው፡፡

ቀደም ባሉ ጊዜያት የክልሉ ሰላምና ደህንነት በተለያዩ አዋኪ ጉዳዮች ሲፈተን እንደነበር ያስታወሱት አቶ ቾንኮት፤ የክልሉ መንግስት ችግሩን ለማስተካከልና የዜጎችን ሠላም ለማስጠበቅ ዘርፈ ብዙ የጸጥታና የደህንነት ስራዎች ማከናወኑን ገልጸዋል።

የጸጥታ ኃይሉ በተቀናጀ መንገድ የሚያከናውናቸው ጠንካራ ስራዎች የዜጎችን ሠላምና ደህንነት ከማስጠበቅ ባለፈ የልማት ስራዎች እንዳይስተጓጎሉ ማድረግ አስችሏል ብለዋል።

በኑዌር እና በአኝዋክ ዞኖች በሚገኙ የክልሉ ኗሪዎች ላይ የሙርሌ ጎሳ አባላት የተለያዩ ጥቃቶችን ለመፈጸም ሙከራዎች ማድረጋቸውን ጠቁመው፤ ሙከራዎቹ በሕዝብና በጸጥታ አካላት ጥምረት መክሸፋቸውን አስረድተዋል።

የሰላምና ደህንነት ጉዳይ ያለኅብረተሰብ ተሳትፎ ውጤታማ እንደማይሆን የገለጹት አቶ ቾንኮት፤ የክልሉ መንግስት በሰላም ግንባታ ዙሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት ከማህበረሰቡ ጋር በተለያዩ ጊዜያት ሰፊ ውይይቶችን እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል። ሰላም እሴት ግንባታዎች ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ ውይይቶች መካሄዳቸው የዜጎች ተሳትፎ ከፍ እንዲል ማድረጉንም አቶ ቾንኮት ጠቁመዋል።

እስካሁን ድረስ በክልሉ የሚታዩ የጸጥታ ችግሮችን በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ለመቅረፍ እየተደረገ የነበረው እንቅስቃሴ ሊበረታታ የሚገባ መሆኑንም ኃላፊው ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ በተገኘው ሰላም ተጠቅሞ በልማት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፍ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን የክልሉ መንግስት ችግሮቹን ለመፍታት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዝግጁ መሆኑን አቶ ቾንኮት በመግለጽ፤ የክልሉ የሰላምና ደህንነት ሁኔታ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በአንጻራዊነት ትልቅ መሻሻል እንዳሳየ አብራርተዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ ጠንካራ የመንግስት መዋቅር በዞንና በወረዳዎች እንዲሁም በማኅበረሰቡ መኖሪያ አካባቢዎች ተፈጥሯል። የጸጥታ ስጋቶች ሲታዩም ፈጥኖ ምላሽ በመስጠት ተደራራቢ ችግሮች እንዳይከሰቱ የጸጥታ ኃይሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደርጋል።

በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩ የታጣቂዎችን እንቅስቃሴዎች በመግታት የሕዝቡን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑንም ጠቁመዋል። አቶ ቾንኮት እንደገለጹት፤ በቀጣይም የጸጥታ አካላት የክልሉን ሰላም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ኅብረተሰቡ የተለመደውን ትብብር ሊያጠናክር ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሳቅ ያለ ጠቀሜታ ሳላቸው አገራዊ እሴቶቻችን ተገቢውን ትኩረትና ቦታ እንስጥ!

ኢትዮጵያውያን ዘመናትን የተሻገረና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያተረፈ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት እና የመቻቻል ባህል ባለቤቶች ነን። ያለው ለሌለው ማካፈል፤ የተቸገረን አይቶ አለማለፍ፤ የታመመ መጠየቅ ወዘተ እንደ ማኅበረሰብ ዘመናትን በፍቅርና በአንድነት ተሻግረን ዛሬ ላይ እንድንገኝ ያስቻሉንና ነገንም እንደሚያሻግሩን ተስፋ የምንጥልባቸው አኩሪ እሴቶቻችን ናቸው።

እነዚህ ለዘመናት አብረውን ከተጓዙ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ እሴቶቻችን የመነጩ፤ ትውልዶች በየዘመኑ በብዙ ማስተዋልና መረዳት ተቀብለው እየተንከባከቡ፤ በተጨባጭም የሕይወታቸው መርህ አድርገው እየተገበሯቸው ፤ ከፍ ያለ መንፈሳዊ እርካታ፣ የሞራል ልእልና እና የሰውነት ልክ የተጎናጸፉባቸው ናቸው።

እነዚህ እሴቶቻችን ዘመኑ ባመጣው ራስ ወዳድነትና ራስ ወዳድነት በፈጠረው ፈተና ዛሬ ላይ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ቢሆኑም፣ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ግን ከልባችን ጓዳ ተጠርገው ያልወጡና በዕለት ተዕለት ሕይወታችን አብዝተን የምናዳምጣቸው፤ የትናንት ያህል የማንነታችን መገለጫ፤ የሰውነታችን ማሳያ አሻራዎቻችን ናቸው።

ዛሬእንደ አገር የኑሮ ፈተና ውስጥ ባለንበት በዚህ ወቅት እንኳን እኛ ኢትዮጵያውያን እራበኝ ለሚል ወንድማችን ከጉድለታችን ለማካፈል፤ ተቸገርኩ ለሚለው ወገናችን ካለችን ከፍለን ለመስጠት፣ የታመመ ጎረቤታችን ባለችን አቅም ለመጎብኘት፣ እግዚአብሔር ይማርህ ብለን የውስጣችንን በጎ መሻት ለመግለፅ አሁንም እየተተገበረ ያለ ማንነት አለን።

እንደ ሕዝብ የመጣንባቸው ውጣ ውረዶች እና ያስከፈሉን መራራ ዋጋ እነዚህን ማህበራዊ እሴቶቻችን የመሸርሸር አቅም አልነበራቸውም፤ ከዚህ ይልቅ በእያንዳንዱ ፈተና እየጠሩ አሁን ላይ ላለንበት ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር አቅም ሆነውናል። አገርም እንደ አገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ጠንክራ እንድትቆም ረድተውናል።

እነዚህን ከፍ ያሉ ማኅበራዊ እሴቶቻችን እንደቀደመው ትውልድ በተሻለ ማስተዋልና መረዳት ልንቀበላቸውና ተጨባጭ የሕይወት መርህ አድርገን በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ልንተገብራቸው ይገባል። በተለይም አሁን እንዳለንበት ወቅት ሕዝባችን በፈተናዎች ለማለፍ ሲገደድ፤ ፈተናዎችን አልፎ ለመሻገር እነዚህን እሴቶቻችንን አቅም አድርገን መሰለፍ ይጠበቅብናል።

አባቶቻችን ትናንት በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፈው ዛሬ ላይ ያለችውን አገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያተረፉልንን ማህበራዊ እሴቶችን ጠብቀው አቆይተውልናል፤ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን አሁን ያለንበት የሕይወት ፈተና እነዚህ እሴቶቻችን እንዲደበዝዙ ምክንያት ሊሆኑ አይገባም፤ እኛም ልንፈቅድ አይገባም።

እነዚህ እሴቶቻችን እንዲደበዝዙና መፍቀድ ማለት በመጪው ትውልድና በአገር ላይ ጥፋት እንደመፈጸም ማለት ነው። ትውልዱ በሕይወት ዘመኑ መንፈሳዊ እርካታ እና የሞራል ልእልና እንዳይኖረው ማድረግ፤ አሁን ዓለምን ክፉና እየተገዳደራት ላለው ራስ ወዳድነት አሳልፎ መስጠት ነው። ይህ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ ዛሬ ላይ ራስ ወዳድነት እያስከፈለን ካለው አገራዊ ዋጋ ብዙም ለመረዳት የሚከብደን አይደለም።

ዛሬ ላይ እኛን ያጋጠመን ፈተና ትናንት ላይ አባቶቻችን ካጋጠሟቸው ፈተናዎች የበለጡ የከበዱ አይደሉም ፤ እያንዳንዱ ትውልድ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ወደፊት ለመሄድ ባለው መሻት መጠን ፈተናዎች ያጋጥሙታል፤ አንዱ ከአንዱ የሚለየው የፈተናዎችን ምንነት ተረድቶ በሚኖረው ዝግጁነት ነው።

ይህ ዝግጁነት ውጤታማ የሚሆነው ከሁሉም በላይ ትውልድን እንደ ትውልድ የሚያሻግሩ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶቻችን ዘመንን እንዲዋጁ የሚያስችላቸውን፤ ማኅበረሰባዊ መስተጋብሮች በተሻለና በዳበረ መልኩ መቀጠል የሚችሉበትን አቅም ማጎናጸፍ ሲቻል ነው። ይህ ደግሞ ለዛሬውና ለነገው ትውልድ ስንል ያለማወላወል ልንተገበረው የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ቋንቋችን ልማት ዓርማችን ደግሞ ሰላም ይሁን

ወጋሶ

ከሰሞኑ የክልል ልዩ ኃይልን አስመልክተው የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰ፣ የክልል ልዩ ኃይል እንደገና ሪፎርም ተደርጎ እንደሚደራጅ መግለጫ መስጠታቸው ይታወቃል። ይህ መልዕክት ከተላለፈ በኋላ ግን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት እየተስተዋለ ያለው ተቀባይነት አዎንታዊም አሉታዊም እየሆነ እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው።

እርግጥ ነው ከዚህ ቀደም በብዙዎች ዘንድ የአገር መከላከያ ሰራዊት እያለ የክልል ልዩ ኃይል ማዋቀሩ ለምን አስፈለገ? በሚል ይቀርቡ የነበሩ ተቃውሞዎችና ትችቶች እንደነበሩ አይዘነጋም። ይሁንና ዛሬ ወደተግባራዊነቱ ሲመጣ ግን ምላሹም ተቀባይነቱም ቀድሞ ከነበረው በተቃራኒው ሆኖ ተስተውሏል። ለዚህ አሉታዊ ምላሽ ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች የተለያዩ እንደሆኑ አስባለሁ።

እንደ እኔ አረዳድ የመጀመሪያው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ከልዩ ኃይሉ ጋር በተያያዘ ያለውን የአደረጃጀትና ሕግ ክፍተት፤ ይህም ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው፤ ሌላው ደግሞ ያልተገቡ ወቅታዊ ስጋቶችን ታሳቢ በማድረግ በየዋህነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው።

ይህ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሲካሄድ ከነበረው ጦርነት ጋር የተያያዘ፤ ጦርነቱ በሰላም ስምምነት ተቋጭቶ ወደሰላም መምጣት ቢቻልም፤ ከፈጠረው ስጋት ጋር ተያይዞ አካባቢያዊ ትንኮሳዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት የሚነሳ ነው ። ይህ የመከላከያ ሰራዊቱ አሁናዊ ቁመናን በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው ብዬ እገምታለሁ።

ዋነኛው ጉዳይ ግን የአገሪቱን ሰላም የማይፈልጉ ግጭት ፈጣሪዎች እና አራጋቢዎች ሥራዬ ብለው፤ የልዩ ኃይሉን መልሶ የማደራጀት ሥራ አጣምመው በማቅረብ ላይ በስፋት መሰማራታቸው ነው፤ ይህ አገሪቱን የሁከት እና የብጥብጥ ማዕከል ለማድረግ ካላቸው መሻት የሚመነጭ።

በርግጥ የክልሎች ልዩ ኃይል የአገር ህልውና አደጋ ውስጥ በወደቀበት ወቅት ከፍ ያለ መስዋዕትነት በመክፈል፤ አገርን በመታደግ ሂደት የጎላ ታሪክ ባለቤት መሆን የቻለ ነው። በዚህም በመንግሥት እና በመላው ሕዝብ እውቅና የተቸረው፤ ዛሬም የሚቸረው ነው። ይህንን ኃይል በአዲስ መልክ ለማደራጀት የተፈለገውም ለበለጠ ዓላማ እና ለትልቅ ተልእኮ እንዲሰለፍ ነው።

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የመንግሥት ውሳኔ፣ ስለአገር የተዋደቀውን እና ትልቅ ዋጋ የከፈለውን ኃይል ‹‹አሁን በቃህ ! አታስፈልገኝም›› የሚል አይደለም። ወይም ደግሞ ‹‹ ከዚህ በኋላ ዕጣ ፈንታህ ትጥቅህን መፍታት እና መበተን ነው ›› የሚል አይደለም ።

ከዚህ ይልቅ በመንግሥት የተነገረውም ሆነ እንዲሆን የተፈለገው ጉዳይ መከላከያን መቀላቀል የሚፈልግ መከላከያን፣ ፌዴራል ፖሊስ መግባት የሚፈልግ ወደ ፌዴራል ፖሊስ እንዲገባ፤ መደበኛ ፖሊስ መሆን የሚፈልገው ደግሞ መደበኛ ፖሊስ እንዲሆን ነው። ከዚህ ባለፈም እስከዛሬ ያለው ይበቃኛል የሚል ካለም በክብር የሚሰናበትበት አሠራር ተግባራዊ የሚያደርግ ነው። ይህ መልሶ ማደራጀቱ የተዋቀረበት የአስተሳሰብ መሠረት ነው።

እንደ እኔ ግንዛቤ፤ የልዩ ኃይል አባላቱ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይልን መቀላቀል ተልዕኳቸውን የበለጠ ከፍ የሚያደርግ፤ የክልላቸውንም ሆነ የአገር አለኝታነትን ከምን ጊዜም በላይ የሚያሳድግ ነው። የአገር ኩራት የመሆንን ዕድል የሚያጎናጽፍም ጭምር ነው።

በተለይ ደግሞ በአህጉር ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሠላም ማስከበር ተልዕኮን ተቀብሎ የሚሰማራ የታላቅ አገር የመከላከያ ሰራዊት አባል

> **ዋነኛው ጉዳይ ግን የአገሪቱን ሰላም የማይፈልጉ ግጭት ፈጣሪዎች እና አራጋቢዎች ሥራዬ ብለው፤ የልዩ ኃይሉን መልሶ የማደራጀት ሥራ አጣምመው በማቅረብ ላይ በስፋት መሰማራታቸው ነው፤**

መሆን ትርጉሙ የቱን ያህል ሰፊና ጥልቅ መሆኑን መገንዘብ የሚከብድ አይደለም።

ይህ እውነታ በእርግጥ አገሩን ለሚወድድ ዜጋ የሚያስደስት እንጂ የሚያስከፋ አይሆንም። ሁሌም ስለአገሩ መሞትን ክብር የሚያደርግ የሰላም ተምሳሌት አርማ የሆነውን የአገር መከላከያን መቀላቀል እንደትልቅ እና መልካም አጋጣሚ ሊታይ የሚገባ ነው።

ከሕግ አንጻርም ቢሆን፤ ክልሎች ከመደበኛ ፖሊስ ውጪ ማደራጀት አይችሉም። የክልል መንግሥት ስልጣንና ተግባርን በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 52 ስር ባለው ንዑስ አንቀጽ 2(ሰ) ላይ እንደተደነገገው፤ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፤ ይመራል፤ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ያስጠብቃል የሚል ነው።

በዚህ መልኩ የየራሳቸውን የፖሊስ ኃይል እንደሚያደራጁ እና የክልሉንም ሰላም እና ጸጥታ እንደሚያስጠብቁ በግልጽ አስቀምጦ እያለ ያልተደነገገ ሕግ ውስጥ ገብተው እስካሁኗ ሰዓት የየራሳቸውን ልዩ ኃይል አዋቅረው ቆይተዋል።

እንዲያም ሆኖ ግን ይህ ልዩ ኃይል የክልሉን ሰላም ከማስጠበቅ ባሻገር በፌዴራል ደረጃ በሚደርሰው ጥሪ መሠረት አገር የጣለችበትን አደራ ሲወጣ እንደቆየም የሚካድ አይደለም። በዚህም ደማቅ ታሪክ ማስመዝገቡ የትናንት ትዝታ ነው።

ይህ ኃይል በአዲሱ አደረጃጀት በተለያዩ የመከላከያና የጸጥታ መዋቅሮች ውስጥ መካተቱ መከላከያ ሆነ ፖሊስ ብሔር የሌለው ከመሆኑ አንጻር ክልልንም አገርንም መጠበቅ የሚያስችል ነው። በክልል ደረጃም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ አለኝታ የሚኮነው ያው ለሕዝብና ለአገር ነውና ልዩነት አይኖረውም።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 87 የመከላከያ መርሆች ተብሎ በተቀመጠው ንዑስ ርዕስ ስር ቁጥር 1 ላይ የአገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ እንደሚሆን በግልጽ የደነገገ ከመሆኑም በተጨማሪ በተግባር መሬት ላይ ያለውም እውነታ ይኸው ነው።

በአገር መከላከያ ሰራዊት ውስጥ መካተት ወይም ደግሞ በፌዴራል ፖሊስ ውስጥ መሆን አሊያም ደግሞ በመደበኛ ፖሊስ ውስጥ መደራጀት ያው ሕዝብንና አገርን መጠበቅ ተቀዳሚ ተልዕኮው ለሆነ አካል የመንግሥት ውሳኔ የሚፈጥረው አዲስ ነገር አይኖርም። የአገርንም ዳር ድንበር፤ የሕዝብንም ሰላም ለመጠበቅ የበለጠ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የተደረገ ውሳኔ ነውና በሪፎርሙና በአደረጃጀቱ መካተት መልካም ነው እላለሁ።

አዲስ አበባ **ሳይንስ** እና **ቴክኖሎጂ** ዩኒቨርሲቲ
ዩኒቨርሲቲ ለኢንዱስትሪ

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና የዩኒቨርሲቲው ቦርድ አመራር ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም በዓሉን ለሚያከብሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንኳን ለ ብርሃነ ትንሳኤ እና ለ2015 ዓ.ም ረመዳን(ኢድ አልፈጥር) በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያሉ በዓሉ የሰላም፣ የደስታ እና የበረከት እንዲሆንላችሁ ይመኛሉ።

**አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ**



# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## «መሆኑ ላይቀር...!?»

«ያ የድል ብስራት ትንሳኤ መሆኑ ላይቀር ስንት ተሞከረ !? የምድር ነገሥታትና የሃይማኖት ጀሌዎች ተማከሩ፤ ሴራ አሴሩ፤ አሾፉ፤ ተዘባበቱ፤ ችንካር ቸነከሩ፤ ጦር ሰበቁ ፤ መቃብር አስጠበቁ ፤ የውሸት ወሬ አስወሩ ፤ ተሰረቀ አስባሉ ግን ገሀድ ሆነ ትንሳኤው በአዋጅ ተበሰረ፤ ብዙዎችን አሻገረ፤ የድል ዜማ ተዜመ፤ ዘሩ በዛ ምድርን ሸፈነች ፤ መላዕክት አሸበሸቡ ዕረፍት ሆነ የቀደመው ጭንቅ ተረሳ። ተፈፀመ። ለአገራችም ዛሬ አርብ ቢሆንም ትንሳኤ ይሆናል። አይቀርም።

ሰላሳ ዓመት የታነፀው ሕንፃ ሦስት ዓመት ተኩል ያገለገለው ቤተመቅደስ ቢፈርስም በሦስተኛው ቀን መነሳቱ ላይቀር ስንት ፋከራ ተፎከረ ግን በትንሳኤው የሁሉም ሴራ ከንቱ ሆኖ ቀረ ። በግለሰብም ፤ በማህበረሰብም በአገርም ደረጃ ትንሳኤ እውን መሆኑ ላይቀር በዲያብሎስ እና በጀሌዎቹ ስንት ምክር ተመከረ፤ ስንት ሴራ ተሴረ ፤ እንዴት ያለ ጥልቅ ጉድጓድ ተቆፈረ ግን ሁሉም ሙከራቸው በጌታና በኃይሉ ችሎት ከንቱ ሆኖ ቀረ ፤ ትንሳኤ ሊበሰር እነሆ ጫፉ ደርሰናል።

ከፉዎች ደግሞ ሬሳዋን ዜጎቿ ሰርቀውት እንጂ ኢትዮጵያ አልተነሳችም ለማለት ሰነድ ሰንደዋል የውሸት አዋጅ ነጋሪዎች በረብጣ ክፍያ አዘጋጅተዋል። ምዕ... መሆኑ ላይቀር ከንቱ መፍጨርጨር። በኋላማ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ይኀሰማል የድል ዜማ እየተባለ በትንሳኤው ኃይል ተነስታለች እማማ። ብዙዎች ይሻገራሉ ከአገር አልፈው ለዓለም ትሩፋት ይሆናሉ የሚሆነው ይህ ነው የሚያምን ይሻገራል የማያምን ግን ይፎገራል።

የኢትዮጵያ ትንሳኤ መሆኑ ላይቀር፤ ማመን እንጂ መጠራጠር ቢቀር፤ አጀንዳው የእግዚአብሔር ነው ተብሎ ቢሰመር ፤ ማለትን እወዳለሁ ። ...» ይሉናል በመንፈሳዊ ጽሑፎቻቸው ከማከብራቸው ጸሐፍት ግንባር ቀደም የሆኑት የውስጥ ደዌ እስፔሻሊስት ሀኪምና በአአዩ የጥቁር አንበሳ የሕክምና ኮሌጅ መምህር ዶ/ር አምሳሉ ቢተው ወርቁ ስለ ትንሳኤው «መሆኑ ላይቀር...!?» በሚል ርዕስ በፌስቡክ ገጻቸው ባስነበቡን አጭር ጽሑፍ።

መጋቢ ኤልደር ዊርዝሊንስ እንዲሁ ሰሞነኛውን ስቅለትና ትንሳኤን ታሳቢ በማድረግ «ዛሬ አርብ ቢሆንም እሁድ ይመጣል ። » የሚል ዘመን ተሻጋሪና ወርቅ ይትበህል ትተውልን አልፈዋል። ጨለማ ፣ የምድር መናዎጥ ፣ ክረምት ፣ ሰደድ እሳት ፣ በረዶ ፣ ጎርፍ ፣ መገፋት ፣ መዋረድ ፣ መገረፍ ፣ መቸንከር ፣ መሰቀል ፣ መከዳት ፣ መሸጥ ፣ መሰቀል ፣ ወዘተረፈ አርብ ቢሆንም፤ መንጋቱ ፣ ብርሃን በጨለማ ላይ መንገሱ ፣ የምድር መናወጥ መቆሙ፣ ብራ ፀደይ መምጣቱ ፣ መከበሩ፣ መፈወሱ ፣ ትንሳኤ ፣ ቀን መውጣቱ ፣ የተሻለ ጊዜ መምጣቱ አይቀርም።

ክርስቶስ ሞትን ድልነስቶ እንደተነሳበት እሁድ ሁሉ ለእኛም ሆነ ለአገራችን ከችግር ፣ ከድህነት ፣ ከተመፅዋችነት ፣ ከኋላ ቀርነት ፣ ከፈተና ፣ ከወረርሽኝ፣ ከጭቆና ፣ ከአፈና ፣ ከጥላቻ ፣ ከጽንፈኝነት ፣ ከጎሰኝነት፣ ወዘተረፈ ነፃ የምንወጣበት አንገታችን በክብር ቀና የምናደርግበት ፤ ትንሳኤ'ችንን ፣ ህዳሴ'ችንን የምናይበት ቀን ይመጣል ። እሁድ ይመጣል ። «ዛሬ አርብ ቢሆንም እሁድ ይመጣል ። » እያልን በእምነት በተስፋ እንጠባበቃለን። ደግሞም ይሆናል ። አርብም አልፎ እሁድ መሆኑና መምጣቱ አይቀረም ይሉናል ሁለቱ ሊቃውንት።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያታችን እና ለበደላችን ክቡር መስዋዕት ሆኖ እንደተሰቀለ ክርስቲያን የተባልን ሁላችን ከልባችን እናምናለን ፤ በየቀኑ እናሰላስላለን፤ በየዓመቱ ደግሞ የተከበረ በዓል አድርገን እናከብረዋለን። ነገር ግን እኛስ ከእርሱ ጋር እንደተሰቀልን እና ዕለት ዕለት መስቀሉን መሸከም እንደሚገባን እናውስተውለዋለን ወይ የሚል

**በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም። በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እንሯሯጣለን እንጂ በሥርዓተ ትምህርታችን አካተን ትውልድን ለማነጽ አላዋልናቸውም። በልቦና ውቅራችን አልተመዘገቡም አልታተሙም**

ብርቱ ጥያቄ ግን ማንሳት እወዳለሁ ይላሉ ዶ/ር አምሳሉ።

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንበት ጊዜ ሁሉ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በቀራንዮ በመስቀል ላይ ሲሰቀል እኛም ከእርሱ ጋር እንደተሰቀልን ማመንን የሚያካትት መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ይህም ማለት አሮጌው ቀዳማዊ አዳማዊ ማንነታችን ፤ የኃጥያት ስጋ እና ራስ ተኮር አካሄዳችን በእርሱ መስዋዕትነት ከእኛ ተወግዷል ብሎ ማመን ነው። ዕለት ዕለት መስቀሉን መሸከም ማለት ደግሞ በዚህ እምነት ነፍሳችንን መስዋዕት ለማድረግ እስከምንደርስ ድረስ በሚያደርግ የእምነት ገድል እየተጋደልን በእርሱ ባለን እምነት መኖር ማለት ነው ። መስቀል እና መሰቀል ከክፉ ደዌ የተገላገልንበት ትምክህታችን ነውና ተገቢውን አንድምታዊ ትርጉም ልናተኩርበት ይገባል ።

መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ «አርብን» እንዳሳለፈ ሁሉ ደረጃው ይለያይ እንጂ በሕይወታችን መውደቅ መነሳቶችን ፣ ህማማትን ፣ አርቦችን አሳልፈናል። ማሳለፋችንም አይቀርም ። በግል ሕይወታችን፣ በትምህርታችን ፣ በፍቅራችን ፣ በትዳራችን ፣ በንግዳችን ፣ በሕልማችን ፣ በራእያችን ፣ በድርጅታችን፣ በሃይማኖታችን ፣ በጤናችን ፣ በቤተሰባችን ፣ በማህበረሰባችን ፣ በሕዝባችን ፣ በአገራችን ፣ ወዘተረፈ ላይ አርብ ሆኖብን (ቀን ጨልሞብን ) እንደ እየሱስ ክርስቶስ ፍርድ ተዛብቶብን ፣ ተገምድሎብን ፣ ታስረን ፣ ተገርፈን ፣ ተሰቅለን ፣ ተቸንክረን ፣ ተዋርደን ፣ ተፈትነን ፣ ባመነው ተክደን ፣ በባልንጀራችን በ ' 33 ' ብር ተላልፈን ተሰጥተን ፣ ሰማይ ተደፍቶብን ወዘተረፈ ይሆናል ። ዛሬም በእነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እያለፍን ሊሆን ይችላል ።

ካለፉት ሁለት መቶ አመታት ወዲህ ያሉትን ጊዜያት እንኳ ብንወስድ እንደ ሕዝብ እንደ አገር ሺህ አርቦችን ፣ በድርቅ ፣ በርሀብ ፣ በቸነፈር ፣ እናት ልጇን እስከ መብላት የተገደደችበት እንደ ክፉ ቀን ያለ እንደ 67ቱ በርሀብ የሞተች እናቱን ጡት የሚጠባበት ፣ እንደ ...77 ... 87 ... ወዘተረፈ ያሉ ጠኔዎችን ፣ ችጋሮችን አሳልፈናል። ዛሬም ከዚህ አዙሪት በቅጡ ሰብረን መውጣት አልቻልንም ። እንደ ኅዳር በሽታ ፣ ፈንጣጣ፣ ከ76 ወዲህ ደግሞ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ፣ በኮቪድ - 19 የእልቂት ተፈትነናል ። በግብፅ ፣ በደርቡሽ ፣ በቱርክ፣ በእንግሊዝ ፣ በጣሊያን ፣ በሱማሊያ ፣ በኤርትራ ተወረናል ። ዛሬም የክተት ነጋሪት የሚያስጎሹምብን አልጠፉም ።

በመቶዎች ሊቆጠሩ በሚችሉ የእርስ በእርስ ግጭቶች አልፈናል። ከዘመነ መሳፍንት እንኳ ብንጀምር በመሳፍንቱ፣ በመኳንንቱ ፣ በነገስታቱ መካከል ለስልጣን፣ ለዘውድ ሲባል በተካሄደ የእርስ በእርስ ግጭት ጦርነት ወገናችን ተጨራርሷል ። አጼ ቴዎድሮስ ፣ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ ፣ ልጅ እያሱ ፣ ንግስት ዘውዲቱ ፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን ፣ መንግስቱ ፣ መለስና ዐቢይም ሆኑ አገራችንና ሕዝባችን ጉዳቱ ፣ ጥፋቱ ይለያይ እንጂ ሁሉም በእርስ በእርስ ግጭት ፣ ጦርነት ተፈትነዋል። የኢትዮጵያ ትንሳኤ መሆኑ ላይቀር ብዙ አርቦችን አሳልፈዋል ። ዶ/ር አምሳሉ ወደ አነሱትና የትህትና ንጉሥ ወደ ሆነው እግር ማጠብ ልመለስ ።

እግርን ማጠብ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲፈፀም የነበረ የመንጻት፥ የአገልጋይነት፥ የትህትና እና የአክብሮት መገለጫ ነው ይሉናል ዶ/ር ። በዘመነ ብሉይ ካህናት የእንስሳት መስዋዕት ለማቅረብ እና ለአገልግሎት ወደ መገናኛ ድንኳኑ ሲገቡ እግራቸውን በመታጠብ ይነጹ ነበር ። በመካከለኛው ምሥራቅ ፥ በአይሁድ እና በኢትዮጵያውያን ዘንድም እንግዳን እግር አጥቦ መቀበል እና ማስተናገድ የተለመደ ሰናይ ተግባር ነው ። በአብዛኛው የእንግዶችን የእግር ማጠብ ተግባር የሚፈፅሙት ደግሞ የቤት አገልጋዮች ነበሩ። ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በአፀደ ስጋ በተመላለሰበት ወቅት የእግር ማጠብን ሥርዓት በመፈፀም አንድምታዊ ምስጢሩን አስተምሮናል፤ እንድናደርገውም አዞናል። ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደ ባሪያ እግራችን ሊያጥብ ጎንበስ ያለውን ንጉሥ እና ጌታ እንደ ጴጥሮስ ለመከልከል መሞከር ተገቢ አይደለም።

የዓለምን ቆሻሻ የሚያስወግደው አንድ ጊዜ የፈፀምነው ጥምቀት ዕለት ዕለት በእምነት በሕይወታችን እንዲሠራ መፍቀድ በዓለማዊነት ከመጠመድ ይጠብቀናል። ይህንንም እንደ መልከ ጸዲቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው ጌታ ያደርገዋል። እግር ማጠብን እርሱ እንዳደረገው እናንተም አድርጉት እንዳለን ዛሬ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ማድረግ ተገቢ ነው። በድፍን ጫማ እንኳን ቢሆን የሚንቀሳቀስን እና ብዙ አቧራ ያልነካውን እግር አጥቦ እንግዳን እና ወንድም እህቶችን ማስተናገድ ተገቢ ቢሆንም መንፈሳዊ አንድምታው ግን ትኩረት ያሻዋል።

፩) በመካከላችን አንዱ ሌላውን እንደ ባሪያ እንዲያገለግለው እና እንድናገለግለው መፈቃቀድ አለብን።

፪) በዓለም ባርነት እንዳንያዝ በመካከላችን በሥራ እና በእውነት የተመሰረተ ፍቅር እና የአንድነት ኑሮ ማጠናከር አለብን ።

፫) እርስ በእርሳችን በምልጃ ጸሎት መተሳሰብ ይገባናል። እኔ እንዳደረኩት እናንተም አድርጉት ያለው ጌታ እንዲሆንልን ጸጋውን ያብዛልን ይላሉ ዶ/ር አምሳሉ። አሜን እያልሁ ፤ ይሄን የፈጣሪ ትዕዛዝ በጀ ብለን አድምጠን በሕይወታችን እየተረጎምነውና እየኖርነው ነው ስል ዛሬም እጠይቃለሁ ።

ቢያንስ ላለፉት 2015 አመታት አዲስ አመትን ፣ መስቀልን ፣ ገናን ፣ ሰሞነ ሕማማቱን ፣ ጸለተ ሐሙስን ፣ ስቅለትንና ትንሳኤን 2ሺህ 15 ጊዜ ያከበርናቸው ቢሆንም የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ጨምሮ በዕለት ተዕለት ኑሯችን ስላልተረጎምናቸውና ስላልኖርናቸው እስከ ዛሬ ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ እርቅን ፣ መነጋገርን ፣ መቀባበልን ፣ መከባበርን፣ መተባበርን ፣ አንድነትን ፣ ወዘተ.እውን ማድረግ አልቻልንም ። አገርን ሕዝብን ከግጭት ፣ ከቀውስ ፣ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር ፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል ፣ ከሴራ፣ ከደባ ፣ ወዘተ . መታደግ አልቻልንም።

እስኪ ለአንድ አፍታ እምነቶቻችንን ወይም ከዚህ አኳይ እንመዝናቸው። ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ሥራ ላይ ውለዋል ! ? አሁን ከምንገኝበት አገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል። ታዲያ እነዚህን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ንብረቶቻችንን እንደ ጦር እቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት ፣ መመላለስ ለምን ተሳነን ? መልሱ ቀላል ነው። ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጂ አንኖራቸውም።

በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም። በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እንሯሯጣለን እንጂ በሥርዓተ ትምህርታችን አካተን ትውልድን ለማነጽ አላዋልናቸውም ። በልቦና ውቅራችን አልተመዘገቡም አልታተሙም። ለብሔራዊ መግባባት ፣ እርቅ ፣ አንድነትና ሰላም ካላቸው ፋይዳ ይልቅ ስለሚሰቡት ጎብኝትና ቱሪስት እንጨነቃለን ። ለእርዱ ፣ ለአውደ አመቱ ፣ ለድግሱና ለፌሽታው ድምቀት ተበድረንና ተለቅተን ሽር ጉድ እንላለን እንጂ ቀኖናውን አልኖርነውም። ይህ የተንሸዋረረ እይታ ሊስተካከል ይገባል።

ባልንጀራህን ፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚሉ አብርሃማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን!? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመን ኢሬቻን በየአመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን? መልሱን ለማግኘት ምስጢሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም። መልሱ ቀላል ነው። እሱም ባህላዊ ንብረቶቻችንን በካዝና ቆልፈን አስቀመጥን እንጂ ሥራ ላይ ስላላዋልናቸው (ኢንቨስት) ስላላደረግናቸው ነው። አገራዊ ሰላምና አንድነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከካዝና አውጥቶ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ በፍጥነት ማፍሰስ ኢንቨስት ማድረግ ይጠይቃል።

ለአገር ግንባታ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ወሳኝ ሚና ከሚጫወተው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሥርዓት በተጨማሪ ለዘመናት እንደ ሕዝብ ፣ እንደ አገር አጋምዶ ያቆየን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ንብረታችን ነው። ሁነቱን፣ ክዋኔውን፣ መንፈሱን ጠብቆ ተንከባክቦና አልምቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ፣ ማስቀጠል፣ ማክበርና ማስተዋወቅ ትልቅ ኃላፊነትም አደራም ነው። ሆኖም የመጨረሻ ግብ ሆኖ ግን ሊወሰድ አይገባም። ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል። አዎ ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ ፤ የሚዋጅና የሚቤዥ መሆን አለበት።

ዘረኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ቂም በቀልን ፣ ደባን ፣ መከፋፈልን ፣ ወዘተ . መቤዥ ፣ መዋጀት አለበት። ባህላዊ ንብረታችንን ይበልጥ በማጎልበት ፣ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ እድላችን ፣ ለነገ ተስፋችን፣ ለእርቅ፣ ለሰላም ፣ ለአንድነት፣ ለሁለንተናዊ ብልፅግና፣ወዘተ. ልናውለው ይገባል። ስኬቶቻችንን የምናወድስበት፣ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አበክረን ማሰብ ያስፈልጋል።

የፍቅር ፣ የእርቅ ፣ የሰላም ፣ የአብሮነት ፣ የማካፈል፣ የመተባበር ፣ የመተጋገዝ ፣ የመረዳዳት ፣ የምስጋና ፣ ወዘተ . ባህሎች ፣ ልማዶች ፣ እምነቶች ፣ ሃይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ንብረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት አገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን ፣ ፍቅር ከጎደለን ፣ እርቅ ከገፋን ፣ ሰላም ከራቀን፣ አብሮነትን በቀዬአዊት ከተካን፣ ማካፈልን በስስት ከቀየርን ፣ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን ፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን፣ ወዘተ . ምኑን ሙሉኡ ሆነው? ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ያለፍንባቸው አገራዊ ውጣ ውረዶች፣ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው ? ስል ለመጠየቅ እገደዳለሁ።

**መልካም የትንሳኤ በዓል !!!**
**ወስብሃት ለእግዚአብሔር!!!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**
**አሜን።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «……እኔ አሁን ያለሁበት ሁኔታ ከሞት የመነሳት ያህል ነው»

- ኢንጂነር ብርሃኑ ጉደታ

እፀገነት አክሊሉ

ሰው መሆን ፈተና ነው የሚሉ አሉ።በመሠረቱ እኔ በዚህ ሀሳብ የምስማማ አይደለሁም።ምክንያቱም ሰው መሆን ማለት ፈተና ሲያጋጥም ተጋፍጦ ማለፍ ብልሀተኛ ሆኖ ነገን ለማየት መሞከር ነው ብዩ ስለማምን ነው።ሰው በሕይወቱ ብዙ መውጣትና መውረዶችን፣ ከፍታና ዝቅታዎችን ያስተናግዳል።ይህንን ደግሞ እንደአመጣጡ ማሳለፍ ይጠበቃል።በዚህ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ደግሞ አንዳንዶች የጠለፋቸው ገመድ እዛው ሊያስቀራቸው እግራቸው ላይ ተጠምጥሞ ይጎትታቸዋል።እሱን በጣጥሰው ያለፉት ያሰቡበት ሲደርሱ ሌሎች ግን ከተተበተቡበት ችግር መውጣት ተስኗቸው የመከራ ዶፍ ለእነሱ ብቻ የመጣ እስኪመስላቸው ድረስ ችግር በአናት በአናት እየተደራረበ መግቢያ ቀዳዳ ሲያሳጣቸው በዚህ መካከል ደግሞ ለችግር እጅ ሰጥተውና ተዳክመው ከገቡበት ቅርቃር መውጣት ተስኗቸው እዚያው የሚቀሩትን ቤት ይቁጠራቸው።

በተለይም ችግር እጅና እግራቸውን አሳስሮ ነገን እንዳይመለከቱ የያዛቸው ሰዎች በችግራቸው ውስጥ ሆነው ራሱ የሚያልፉባቸው ነገሮች በጣም ከባድ ሲያልፍም አሳዛኝ የሚሆኑበት ጊዜ ብዙ ነው።ግን ደግሞ ሁሉም ችግር፤ ችግር ሆኖ የሚቆየው ለጥቂት ጊዜ ነውና በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ከችግራቸው ወጥተው አንዳንዴም ዳግም ተወልደው ይታያሉ።


በአገራችንም ቀን የጎደለባቸው በተለያየ ምክንያት ኑሮ ፊቷን ያዞረችባቸው ሰዎች ብዙ ናቸው።ደጋጎች አግኝተዋቸው ከችግር ሲያላቅቋቸው ሌሎች ደግሞ ባሉበት እዚያው ቀናቸውን እየጠበቁ የሚከርሙም ጥቂት የሚባሉ አይደሉም።

እኛም ለዛሬ የሕይወት ገጽታ አምዳችን እንግዳ ያደረግናቸው ኢንጂነር ብርሃኑ ጉደታን ሲሆን ብዙ የተማሩ አገራቸውን በብዙ ያገለገሉ በማገልገል ላይም የነበሩ ነገር ግን የሕይወት መስመር ባልጠበቁት ሁኔታ ተዛብቶባቸው ከሥራቸው፣ ከኑሯቸው፣ ከማህበራዊ ግንኙነቶቻቸው በአጠቃላይ ሰው ሊያደርገውና ሊሆነው ከሚገቡ ነገሮች ሁሉ ርቀው ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው ጎዳና እስከማደር የደረሱ ናቸው።ይህም ቢሆን ግን አንዱ በር ሲዘጋ ሌላው ይከፈታልና ኢንጂነሩ ጎዘናቸው በዝቶ መኖር አስጠልቷቸው በደረሰባቸው ችግር አእምሯቸው መደበኛ ሥራውን እስከማቆም ደርሶ የጎዳና ተዳዳሪ ቢሆኑም ቅሉ፤ ለአገር ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ያወቁ ደጋጎች ከጎዳና ይነሱ፤ እንደ ቀድሞው ወደሙሉ ጤንነታቸው ተመልሰው ለአገር ለወገን የሚጠቅም ሥራን ይሠሩ ዘንድ ወደ መቄዶንያ አመጧቸው።ዛሬ ኢንጂነር ብርሃኑ ጉደታ ዳግም ተወልደዋል።

ኢንጂነር ብርሃኑ ጉደታ ከወታደር አባታቸውና ከአርሶ አደር እናታቸው የተወለዱት ደብረ ሊባኖስ ነው።ነገር ግን ኢንጂነር ብርሃኑ በተወለዱበት አካባቢ ከእናት ከአባታቸው ጋር የማደግን ዕድል አላገኙም።ምክንያቱ ደግሞ አባታቸው ሌላ ትዳር በመመስረታቸውና እሳቸውን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ሰፈር በመምጣታቸው ነው።

«……የተወለድኩት ደብረ ሊባኖስ ነው፤ ነገር ግን ብዙም እዚያ ሳላድግ በልጅነት ዕድሜዬ ነው ከተወለድኩበት ቀዬ የወጣሁት፤ ያደኩትም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩትም አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ነው።በመሆኑም ደብረ ሊባኖስን ተወለድኩበት እንጂ አላደኩበትም» ይላሉ።

የወታደር ልጅ የሆኑት ኢንጂነር ብርሃኑ ከትምህርት ዓለም ጋር የተዋወቁት በአባታቸው ጓደኛ አማካይነት በቄስ ትምህርት ነበር።የቄስ ትምህርቱን ሲማሩ የትምህርት ፍላጎታቸው፤ አቀባበላቸው ሁሉም ነገር ከእኩዮቻቸው ሁሉ የተለየ እንደነበር የሚያስታውሱት ኢንጅነር ብርሃኑ በዚህም እስከ ወንጌል ድረስ ያለውን የቄስ ትምህርት ፕሮግራም በሚገባ ስለማጠናቀቃቸው ይናገራሉ።



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

የቄስ ትምህርቱን እንዳጠናቀቁም የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመጀመር ያቀኑት በቀድሞ ጊዜ ልዑል ራስ ስዩም (ሕዝባዊ ሠራዊት) የሚባል ትምህርት ቤት ነው።በዚህም እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርታቸውን የተማሩ ሲሆን አራተኛ ክፍል እንዳጠናቀቁ ግን በልጅነታቸው አባታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ የሕይወት አቅጣጫቸው ሌላ መስመርን ይይዝ ዘንድ ግድ ሆነ በዚህም ኢንጅነር ብርሃኑ ጉዟቸውን ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ አደረጉ።

«……በወቅቱ እናትም አባትም ስላልነበረኝ አባቴም ወታደር ስለነበር  አዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ ይገኝ ወደነበረው ሕፃናት ማሳደጊያ እንድገባ ሆንኩ።የትምህርት ደረጃዬም ከአራተኛ ክፍል ወደ አምስት ያለፍኩበት ነበርና በማሳደጊያው ሆኜ ትምህርቴን በአግባቡ እየተከታተልኩ አምስተኛና ስድስተኛ ክፍልን በማሳደጊያው ሆኜ ተማርኩ» ይላሉ ።

ሰባተኛ ክፍል ሲደርሱም በማሳደጊያው አቅራቢያ ይገኝ የነበረው በቀድሞ ስሙ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ኋላም ምሥራቅ በር ቁጥር 1 ትምህርት ቤት በመግባት የሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ስለመማራቸው ይናገራሉ።ኢንጂነር ብርሃኑ በትምህርት ቤት ቆይታቸው በጣም ጎበዝ የሚባሉ ባይሆኑም እስከ አስረኛ ድረስ ያለውን ደረጃ በመውጣት ግን ትምህርታቸውን ይከታተሉ እንደነበር ያስታውሳሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ሊከታተሉ ያቀኑት ምሥራቅ አጠቃላይ ወደሚባል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር።ነገር ግን እዚህ እየተማሩ ባሉበት ወቅት በተለይም ከዘጠነኛ ወደ አስረኛ ክፍል ሲያልፉ ሌላ የሕይወት መስመር ተከፈተላቸው።እሱም መንግሥት የወታደር ልጆች የሆኑትን ከሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በመሰብሰብ የውጭ አገር የትምህርት እድል እንዲያገኙ እያደረገ ነበርና ኢንጂነር ብርሃኑም የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆኑ።

«…….. የሕፃናት ማሳደጊያ በተለይም እኔ የነበርኩበት ቦታ ላይ በሁለት ዙር ወደ ውጭ አገር ሄደን እንድንማር እድል ተሰጠ።የመጀመሪያው ዙር በ1970 ዓ.ም የሄዱ ሲሆን ሁለተኛው ዙር ደግሞ በ1971 ዓ.ም እኛ ወደ ኩባ ሄደን ትምህርታችንን እንድንከታተል ሆንን» ይላሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ ኩባን በተለያየ መንገድ ይገልጿታል።በተለይም ለኢትዮጵያ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ገልጸው አይጨርሱትም ።ኩባ በሱማሌ ጦርነት ጊዜም አጋራችን ስለነበረች የእኛን ጀግንነት ሰው አክባሪ መሆንና ሌላውንም ነገር ታውቃለች፤ በዚህም ኢትዮጵያውያንን በተለየ ትኩረት ነው የምታየው ይላሉ።

«…….ኩባዎች ለኢትዮጵያውያን ጥሩ አመለካከት አላቸው የአገሪቱ መሪ የነበሩት ፊደል ካስትሮም ከደርግ መንግሥት አስተዳደር በተለይም ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ጥሩ ቁርኝት ያላቸው ስለነበሩ ሕዝቡ ላይም ይህ ስሜት ተጋብቶ ለኢትዮጵያውያን ለየት ያለ ፍቅር አላቸው» ሲሉ ይገልጿቸዋል።

ኢንጂነር ብርሃኑና ጓደኞቻቸው ኩባ እንደደረሱ ትምህርት ቤት የገቡት የአገሪቱን መግባቢያ ቋንቋን የሆነው ስፓኒሽ ለመማር  ነበር።በዚህም ለአንድ አመት ያህል የቋንቋ ትምህርቱን ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ በቀጥታ ያመሩት ወደ ትምህርት ነበር።ከዛም  የአስረኛ ክፍል ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ።

በኩባ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ቀጠሉ።ኢንጂነር ብርሃኑ የኩባ ትምህርት ከኢትዮጵያ የትምህርት አሰጣጥ ጋር በብዙ እንደሚገናኝ ያነሳሉ።በተለይም «ትምህርቱ ለማወቅ ብዙ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑ፤ ፈተናውም የተማርነውን በጽሑፍ እንድንገልጽ እንጂ ምርጫ ብሎ ነገር የሌለው መሆኑ ከአገራችን ትምህርት ጋር ይገናኛል» ይላሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ ይህም ቢሆን ግን በቻሉት መጠን አብረዋቸው ከሄዱት ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ሆነ እዛው ኩባ እየኖሩ ከሚማሩ የተለያየ አገር ዜጎች ተማሪዎች እንዳያንሱ ሌት ተቀን ይሠሩ ነበር፤  ይህም በትምህርታቸው ላቅ ያለ ውጤትን እንዲያመጡ አግዟቸዋል።

«……ኩባ የምንኖረው እዛው አንድ ቦታ ላይ አንድ ካምፕ ውስጥ ነው።ወዴትም አንሄድም።ምግብና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችም ይቀርቡልናል። ከዚህ አንጻር ደግሞ እኛ የሚጠበቅብን በትምህርታችን ላይ ትኩረት ማድረግ ብቻ ነበር»  በማለት ይናገራሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ በኩባ ከአስረኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያለውን የትምህርት ቤት ቆይታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በቀጥታ የገቡት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም (ዩኒቨርሲቲ ) ነበር።

«……..ዩኒቨርሲቲም ትምህርቱ ቀላል አልነበረም።ብዙ ማንበብ መሥራት የሚጠይቅ ነበር።ውጤታማ ለመሆንም  ሌት ተቀን አንብበዋል።ያም ቢሆን ግን የኮምፒዩተር እና የሒሳብ ትምህርትን መርጬ ተማርኩ።ሁለቱ በአንድ ላይ የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ስለነበሩ በድል ለማጠናቀቅ ከፍ ያለ ጥረትን አደረኩ።እናም ፈጣሪ ይመስገን ተሳካልኝ» ይላሉ ኢንጂነሩ፡፡

በኩባ እነ ኢንጂነር ብርሃኑ ብቻ አልነበሩም የወቅቱ ተማሪዎች።በአገር ውስጥ አስራ ሁለተኛ ክፍልን በማጠናቀቅ በተለያየ መንገድ ኩባ ደርሰው ትምህርታቸውን የጀመሩ በርካቶችም ነበሩ።ከእነሱም ጋር «የአገር ልጅ የማር እጅ» እየተባባሉ ጥሩ ግንኙነት እንደነበራቸውም ኢንጂነር ያስታውሳሉ።ከሁሉም በላይ ግን የአምስት አመት የኩባ የትምህርት ቆይታቸውን የማይረሱት፤ እጅግም የሚወዱት እንደነበረ ጨምረው ይናገራሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ እንደሚሉት ኩባዎች ለአምስት ዓመት ያህል አስተምረው የሚሰጡት የትምህርት ማስረጃ የማስትሬት ዲግሪ ሲሆን ከኢትዮጵያ ዲግሪ ጋር እኩል ነው።ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ትምህርቱ በንድፈ

# የሕይወት ገጽታ



ሃሳብም በተግባርም የሚሰጥ ስለነበር ለእኛ በቂና ተገቢ እውቀት ያስጨበጠ ነበር።

ኢንጂነር ብርሃኑ ወደአገራቸው እንደተመለሱ የሥራውን ዓለም ‹‹ሀ›› ብለው የተቀላቀሉት ትምባሆ ሞኖፖል በሚባለው ተቋም በሂሳብ ሠራተኝነት ነው።በመሥሪያ ቤቱም በ 500 ብር ደመወዝ ተቀጥረው የሂሳብ ሥራውንም በአግባቡና በሥርዓቱ እየሠሩ ኑሮን መግፋት ያዙ።

«........ ከኩባ እንደተመለስኩ ቤት ተከራይቼ ሥራዬንም በትምባሆ ሞኖፖል ጀምሬ በማገኘው ደመወዝ እራሴን እያስተዳደርኩ በጥሩ ሁኔታ ነበር የምኖረው ።እውነት ለመናገር ቤተሰብ እንደሌለኝ እንኳን ተሰምቶኝ አያውቅም ነበር» ይላሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ እድል ከእሳቸው ጋር ናትና በትምባሆ ሞኖፖል ለሦስት አመት ያህል እንዳገለገሉ መንግሥት የወታደር ልጅ መሆናቸውን በመገንዘብ ለተጨማሪ ትምህርት በሚል ነፃ የትምህርት እድል አመቻችቶ ወደ ምሥራቅ ጀርመን ላካቸው።

«......አዎ እድለኛ ነኝ ማለት ይቻላል።ሥራ ተቀጥሬ ገና በሦስት አመት አገልግሎቴ ተጨማሪ ትምህርት ተምረህ ና ብሎ መንግሥት ወደ ምሥራቅ ጀርመን ላከኝ። ይህ ለእኔ ትልቅ እድል ነበር።በጣምም ደስተኛ ሆኜ ነው የሄድኩት» ይላሉ።

ወደ ምሥራቅ ጀርመን ያቀኑት ኢንጂነር ብርሃኑ የኢንጂነሪንግ ትምህርታቸውን ወዲያውኑ ነበር የቀጠሉት።‹‹እዛም ጥሩ ቆይታን አሳለፍኩ›› ይላሉ።

«......መንግሥት የወታደር ልጅ ብሎ ዳግም ነፃ የትምህርት እድል ከአገር ውጪ ሲሰጠን በጣም ነበር ደስተኛ የሆንኩት።በተላኩበት አገር ላይም በሲቪል ኢንጂነሪንግ የትምህርት መስክ ጉዞዬን አንድ ብዬ ጀመርኩ።ጥሩው ነገር ቀድሞም የኩባ ተማሪ ስለነበርኩ የውጭው ዓለም ምን እንደሚመስል አዲስ አልሆነብኝም። እናም በቀጥታ ወደ ትምህርቴ ገብቼ ትኩረቴን በትምህርቴ ላይ ብቻ ነበር ያደረኩት» በማለት ሁኔታውን ይገልጹታል።

ሦስት የትምህርት ዓመታትን በመልካም ሁኔታ እንዲሁም በጥሩ ውጤት አጅበው ያጠናቀቁት ኢንጂነር ብርሃኑ ወደ አገራቸው ከተመለሱም በኋላ ቀድመው

**«........መቄዶኒያ እኔን እንደገና ነው የወለደኝ።ቢኒያም መልካም ሰው ነው።ባለቤቱ እሌኒም ስለእኛ እንዴት እንደምታስብና እንደምትከታተሰን እኔ ነኝ የማውቀው**

ይሠሩበት ከነበረው ትምባሆ ሞኖፖል መስሪያ ቤት በሥራ እንዲቀጥሉ ሆነ።

«........የትምህርት ሁኔታዬን አሻሽዬ ስመጣ መስሪያ ቤቱ በጥሩ ሁኔታ ነበር የተቀበለኝ።እንዲያውም የደረጃና የደመወዝ እድገት ሁሉ አግኝቼ ነበር።በዚህም በጣም ደስተኛ ሕይወት እየመራሁ ባለሁበት ሁኔታ ግን አሁን ላለሁበት ችግር ወዳበቃኝ ታሪኬ ገባሁ» ይላሉ እጅግ ባዘነና በተሰበረ ሁናቴ።

ኢንጂነር ብርሃኑ ከሥራ ወደ ቤት ከቤት ወደሥራ መመላለስ የዘወትር ተግባራቸው ነበር። አሁን ትምህርቱ ዳር ደርሷል።ጥሩ ደመወዝም ተከፋይ ናቸው።የቀራቸው ነገር ቢኖር አንድና አንድ ነው።እሱም ጎጆ ቀልሶ ልጆች ወልዶ መኖር።ይህንን ሃሳብ ደግሞ ሁሌም ያስቡታል።የብቸኝነት መንገዱ ባማረራቸው ቁጥር ፈጣሪያቸውንም ውሃ አጣጭ እንዲሰጣቸው መለመናቸው አልቀረም።ለሁሉም ጊዜ አለውና እሳቸው ፈጣሪያቸውን እየጠየቁና የራሳቸውን አንዳንድ ሙከራዎች እያደረጉ ቀናቶች መቆጠራቸው አልቀረም።

ታዲያ ከዕለታት በአንዱ ቀን ኢንጂነር ብርሃኑ ወደ ፈጣሪያቸው ያስገቡት ማመልከቻ ምላሽ ያገኘ የሚመስልበት አጋጣሚ ተፈጠረ።አዘውትረው ከቤት ወደ ሥራ ማታም ከሥራ ወደቤት በሚመላለሱበት ጎዳና ላይ እንደሳቸው ሁሉ ጠዋት ለሥራ ማታ ደግሞ ወደቤት የምትሄድ መልከ መልካም ወጣት ማየት ጀመሩ።ይህ ሁኔታ ቢያስደስታቸውም የልጅቱን ማንነትና ምንነት እስከሚያውቁ ድረስ ጊዜ መውሰዳቸው አልቀረም።

እሳቸውና ወጣቷ እየተያዩ ቀናቶች እንደዋዛ ተቆጠሩ።በዚህ መካከል ግን ኢንጂነር ይህችን ልጅ ሳልቀደም ማናገር የግሌ ማድረግም አለብኝ ብለው በመነሳት አነጋገሯት።ልጅቱም ቀልቧ ወዷቸው ነበርና ቀጥተኛ የእሺታ መልስ ባትሰጣቸውም አልፈልግም ብላ ደግሞ ለመገፍተር አቅም አልነበራትም።በዚህ መካከልም ኢንጂነር መውጫ መግቢያዋን እየጠበቁ ማዋራት፤ ለመቀራረብ መሞከር ያዙ።ያሰቡት ተሳካናም ከልጅቱ ጋር ጥሩ መግባባት ውስጥ ደረሱ።ይህ መግባባት ደግሞ ውሎ አድሮ ወደፍቅር ተለወጠ።እሳቸውም እሷም እልም ያለ ፍቅር ውስጥ ገቡ።በዚህም አንዳቸው አንዳቸውን ሳያዩ መዋል ማደር አስቸጋሪ ሁሉ ሆነባቸው።

ይህ ፍቅራቸውና መተሳሰባቸው ደግሞ አድጎና ጎልብቶ ለምን በአንድ ቤት ተጠቃለን እንኖርም (አንጋባም) ወደማለት አደረሳቸው።ኢንጂነር ቀድሞውንም ውሃ አጣጭ ፈላጊ ነበሩና ይህንን ስሜት ማሳለፍ አልፈለጉም።በቶሎ የወደዷትን ቆንጆ ወጣት እጃቸው አስገቡ፤ በትዳርም ተሳሰሩ።

«.......ባለቤቴን ያገኘኋት ሁሌ በምመላለስበት አካባቢ ነው።ደጋግሜ ማየቴ ደግሞ ፍቅር ውስጥ ጨመረኝ።እሷም ለጥያቄዬ ተገቢውን ምላሽ ሰጥታኝ አብራኝ ለመኖር አላቅማማችም ነበር።በዚህም በጣም ደስተኛ ሆንኩ።እሷም ትሠራለች፤ እኔም እሠራለሁ።ኑሯችንም ጥሩ ነበር» በማለት ያስታውሳሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑና ባለቤታቸው በትዳር ተሳስረው ለአስር ዓመታት ቆዩ ። በእነዚህ ዓመታት ግን የአብራካቸውን ክፋይ አግኝተው ለመሳም አልታደሉም።ያም ሆኖ ግን የጸናው ፍቅራቸውና እምነታቸው ሳይነቃነቅ ነገ የተሻለ ይሆናል በሚል ጥሩ ስሜት አመታትን በፍቅር አሳልፈዋል፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ ግን ኢንጂነር ብርሃኑና ባለቤታቸው ለአመታት በጽናት ሲጠብቁት የነበረ ክስተት ሆነ።ሚስት ጸነሱ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ በእሳቸውና በባለቤታቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በሚያውቋቸው ሰዎች ሁሉ ደስታን ፈጥሮ ነበር።ፈጣሪ ምን ይሳነዋል ሲል ሁሉም ለእነሱ ደስታውን ገለጸ።ዘጠኙ ወራትም በጥሩ ሁኔታ አለፉ።ባልም ነፍሰ ጡር ሚስታቸውን እየተንከባከቡ በደስታ ዘለቁ።ነገር ግን ደስታው ደስታ ሆኖ ሊዘልቅ አልቻለም።ሚስት ቀናቸው ደርሶ ለመውለድ ሆስፒታል ሄዱ።ነገር ግን የተጓጓለትን ልጃቸውን አቅፈው ወደ አስር ዓመት የትዳር ጎጆቸውና ወደሚወዷቸው ባለቤታቸው መመለስ ሳይችሉ ቀሩ።በወሊድ ምክንያት ሕይወታቸውን አጡ።ኢንጂነር ብርሃኑ ሚስታቸውን ማጣታቸው ሳያንስ ለአመታት በጉጉት የጠበቁትን የአብራካቸውን ክፋይ እንደ አባት ለማቀፍ ሳይታደሉ ቀሩ።እናትና ልጅ ጥለዋቸው ወደፈጣሪያቸው ሄዱ።

«........ ባለቤቴና እኔ ከብዙ ዓመታት ጥበቃ በኋላ ያገኘነውን ልጅ አቅፈን ለመሳም ሳንታደል ሁለቱም እኔን ብቻዬን ጥለውኝ ሄዱ።በዚህ ምክንያት ደግሞ እኔ አእምሮዬን ሳትኩ።ምንም መረጋጋት የሚባል ነገር ላገኝ አልቻልኩም።ሁኔታው ከአቅሜ በላይ ሆነ አበድኩ» ይላሉ ኢንጂነሩ በጊዜው የተፈጠረውን ሁኔታ ሲያስታውሱ።

ኢንጂነር ብርሃኑ ይህንን መሰል አጥንት የሚሰብር፤ ልብ የሚያደማ እንኳን ለደረሰበት ለሰማውም የሚከብድ ዜና መቋቋም አቃታቸው ።ምንም እንኳን ሥራ ብለው ጠዋት ከቤታቸው ቢወጡም የሚሠሩት አይገባቸውም።ሰውም ሲያናግራቸው ሊያጽናናቸው ቢሞክረም እሳቸው ግን ከልባቸው አልነበሩም።ምን እየተካሄደ እያለ እንኳን ማወቅ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ ።መስሪያ ቤታቸው የአብሮ አደግ የሕፃናት ማሳደጊያ ልጆች እንዲሁም ኩባ አብረዋቸው የተማሩና ሌሎች የሚያውቋቸው ሁሉ ከዚህ ልብ ሰባሪ የኀዘን ስሜት ውስጥ እንዲወጡ ከፍ ያለ ጥረትን ቢያደርጉም እሳቸው ግን ሁኔታውን መርሳት ሳይችሉ ቀሩ።

«.......የኩባ ተማሪዎች እንዲሁም የሚያውቁኝ የወታደር ልጆች ከሚገባው በላይ እንክብካቤን አደረጉልኝ። እኔ ግን ወደራሴ ለመመለስ ሳልችል ቀረሁ።ቆይቼም ሥራዬን አቆምኩ ።መጨረሻዬም ጎዳና ላይ መውጣት እጣ ፈንታዬ ሆነ» በማለት ልብ የሚሰብር ታሪካቸውን ይናገራሉ።

ኢንጂነር ብርሃኑ ጎዳና ላይ ሆነውም የሚያስቡት ባለቤታቸውን ሳያዩት ሳይነኩት ያጡትን ልጃቸውን ነበር።ባደጉበትና በኖሩበት ፈረንሳይ ለጋሲዮን ላይም ሦስት ያህል አመታትን ጎዳና ተኙ።በእዚህ ጊዜ የሚያውቋቸው የሰፈራቸው ሰዎች እንዳይርባቸውና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይጠብቋቸው ነበር።

ኢንጂነር ብርሃኑ የገቡበት ጭንቀት የአእምሮ ህመም ውስጥ አስገባቸው።ይህ ሁኔታቸው ያሳሰባቸው ብሎም ድሮ የሚያውቋቸው ጓደኞቻቸው ምን ማድረግ አለብን ብለው ሲያስቡም ኢንጂነር በቋሚነት የሚረዱበት ሁኔታ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብና በመነጋገር ወደ መቄዶኒያ የአረጋውያንን የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል እንዲገቡ ሆነ።

«ጓደኞቼ ኢንጂነር አሰጋ ገበየሁ፣ ኢንጂነር የብራ መሃሪና ኢንጂነር መስፍን መንግሥቱ በመነጋገርና በመተባበር መቄዶንያ እንድገባ አገዙኝ።ወደ ማዕከሉም ከገባሁ በኋላ ጥሩ ሕክምና አገኘሁ።ያለፍኩበትንና የደረሰብኝን እንድረሳ በርካታ የሥነ ልቦና እገዛ ተደረገልኝ» በማለት ይናገራሉ።

ኢንጂነር በአሁኑ ወቅት መቄዶንያ ውስጥ ክሊኒክ፣ ፋይናንስ፣ ላይ በማስተባበርና በጥበቃ እንዲሁም አሁን ላይ ደግሞ የስልክ ኦፕሬተር በመሆን ተቋሙን እያገለገሉ ይገኛሉ።

«........መቄዶኒያ እኔን እንደገና ነው የወለደኝ።ቢኒያም መልካም ሰው ነው።ባለቤቱ እሌኒም ስለእኛ እንዴት እንደምታስብና እንደምትከታተለን እኔ ነኝ የማውቀው።ሠራተኞቹም ከሚገባው በላይ ነው እንክብካቤያቸውን የሚያደርጉልን።በጠቅላላው የፍቅር ቤት ነው ቢባል የሚያንሰው እንጂ የሚበዛበት አይደለም» ይላሉ።

«......እኔ አሁን ያለሁበት ሁኔታ ከሞት የመነሳት ያህል ነው።ጎዳና ሆኜ አስተውላቸው የነበሩ ነገሮች በሙሉ ከባድና አስቸጋሪ ናቸው።ምንም እንኳን አእምሮዬ ጤነኛ የነበረ ባይሆንም አሁንም ድረስ ግን ሳስባቸው የሚዘገንኑኝ ድርጊቶች በጎዳና ላይ ይፈጸማሉ።ከዚህ ሁሉ ነገር ወጥቼ ደግሞ ዛሬ ላይ እዚህ በመድረሴ ለዚህ ያበቁኝን ጓደኞቼን ከምንም በላይ ግን መቄዶንያን በጣም አመሰግንለሁ» ይላሉ።

ዛሬ ላይ ኢንጂነር በጤናቸው ላይ መልካም የሚባል ለውጥን አይተዋል፤ እየሠሩም ነው።ነገር ግን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ተሽሏቸው ከእንቅልፍ ኪኒን ወጥተው እንደ ማንኛውም ሰው መተኛትና መነሳት በትክክል ነገሮችን ማገናዘብ ሲችሉ በተቋሙ ውስጥ የተሻለ ሥራን ለመሥራትና አቅማቸውና እውቀታቸው የፈቀደውን ሁሉ ሠርተው እንደሳቸው ሳያስቡት ችግር ውስጥ ለሚገቡ ብሎም ጧሪ ቀባሪ ለሌላቸው ምስኪኖች መቆም ህልማቸው ነው።

ኢኮኖሚ

## ባህልና ቱሪዝም

# የትንሳኤ በዓል ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ በበርካታ የታሪክ፣ የባህል፣ የአስተሳሰብ፣ የፎክሎርና የጥበብ እሴቶች የተገነባች አገር ነች። ከሦስት ሺህ ዘመናት በላይ ሕዝቦች የጋራ ማንነት ኖሯቸው አብሮነታቸው የጠነከረ እንዲሆን ያስቻሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶች ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገሩ እዚህ ደርሰዋል። ለዚህ ነው «ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የባህል መናገሻ» እንደሆነች የሚገለጸው።

ሕዝቦቿ በብዙ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ተከብበውና ተዋድደው የሚኖሩ የፍቅርና የመከባበር ተምሳሌቶች እንደሆኑም ይነገራል። አገሪቱ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያስከብሩ የራሷ የዘመን መቁጠሪያና ፊደል ያላት፤ በሌላው ዓለማት በማይገኙና ተወዳጅ በሆኑ በዓላት፣ አልባሳትና የአመጋገብ ሥርዓትም ትታወቃለች።

የፎክሎር ባለሙያው ዶክተር ዘላለም ተፈራ ግብረ ገብነት፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት፣ ሰብዓዊነት የኢትዮጵያውያን መገለጫና አብሮ የመኖር ተምሳሌት መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። «የባህል እሴቶቻችን በትውልድ መካከል የሚኖር ተግባቦትና የሚደረግ ቅብብሎሽ ምን መሆን አለበት?» ለሚለው ጉዳይ ምላሽ ሲሰጡም ሰው የመሆን ክብር፣ ከራስ ባሻገር ለሰው ቅድሚያ መስጠት እንደሆነ ይጠቅሳሉ።

በርካታ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራንም ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ከመሆኗ አንፃር የዚያኑ ያህል እጅግ ብዙና ህብርን የተላበሱ እሴቶችና የጋራ ማንነቶችም እንዳሏት በተደጋጋሚ ይገልፃሉ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሀገር ልማት ጥናት ኮሌጅ ዲን የሆኑትና በቱሪዝም ልማትና አስተዳደር፣ በቱሪዝም ምርቶችና ሌሎች መሰል ጉዳዮች ላይ በማስተማር፣ ከማስተዋወቅ አንፃርም ምርምርና ጥናት ለፖሊሲ ግብአቶች በማበርከት የሚታወቁት ዶክተር ተስፋዬ ዘለቀ የዚህ ሃሳብ ተጋሪ ናቸው። ዜጎች ከሃይማኖታቸው ከሚቀዱ የበዓል ሥርዓቶች የተገነባ ውብ ማንነት ከመላበሳቸውም ባሻገር፤ በመቻቻል ለዘመናት አብሮ በመኖር በዳበረው እሴት የተነሳ ሁሉም የሚጋሩት ባህልና ኢትዮጵያዊ ቀለምም እንዲሁ መገለጫው እንደሆነ ይናገራሉ። ከእርሳቸው በተጨማሪ ከላይ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የማህበራዊ ዘርፍ ምሁራን ሃሳቡን በተጨባጭ ማስረጃ ያረጋግጡልናል።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን መለወጫ እስኪበሰር ድረስ «ከመስከረም እስከ መስከረም» አያሌ ተወዳጅና በጉጉት የሚጠበቁ ክብረ በዓላት፤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች ይካሄዳሉ። ከዘመን መለወጫ ወይም እንቁጣጣሽ እስከ «መስቀል»፣ ኢሬቻ፣ ጨምበላላ፣ ጥምቀት፣ ጊፋታ እና ሌሎችም በርካታ የማህበረሰቡን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች የሚያሳዩ ተወዳጅ እሴቶች በድምቀት ይከበራሉ። ከውጪ ሆኖ ለሚመለከታቸው በሚያስቀኑና «የኔ በሆኑ» በሚያሰኙ ኢትዮጵያዊ ህብር ማንነቶች ዜጎች አብረው በጋራ ይደምቃሉ።

በመግቢያችን ላይ በምሁራን ከተገለጹት ኢትዮጵያዊ እሴቶች መካከልም በተያዘው የሚያዝያ ወር በክርስትና እምነት ተከታዮችና በእስልምና አማኞች ዘንድ የሚከበሩት «የትንሳኤና» እና «የረመዳን» ታላላቅ ሃይማኖታዊ በዓላት ይገኙበታል። ዛሬ በመላ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እየተከበረ የሚገኘው የትንሳኤ በዓል በአገሪቱ ከሚከበሩ ተወዳጅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥነሥርዓቶች ውስጥ አንዱ ነው።

በእሉ ሃይማኖታዊ ብቻም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ባህላዊ እሴቶች በድምቀት የሚንጸባረቁበትም ነው። ይህ በዓል በባህሪው ለአንድ ቀን ብቻ የሚከበርም አይደለም ለአንድ ሳምንት በተለያዩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶች በድምቀት ይከበራል፡፡

የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት በአብዛኛው ከባህላዊ ሥርዓቶች ጋር ከፍተኛ ትስስር አላቸው። የአመጋገብ፣ አለባበስ፣ መረዳዳት፣ ቤተሰባዊ አብሮነትና ፍቅር ከሃይማኖታዊ በዓላት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው።

ለምሳሌ ያህል በዛሬው እለት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እየተከበረ ከሚገኘው የእየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ወይም «የፋሲካ በዓል» ጋር የሚገናኙ አያሌ ባህላዊ ሥርዓቶች አሉ። በተለይ ይህ ክብረ በዓል ከመድረሱ አስቀድሞ የሃይማኖቱ ተከታዮች በእለቱ በድምቀት ለሚከወነው ሥርዓት የሚያደርጉት ዝግጅት በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ባህላዊ ውበትና ድምቀትን የሚፈጥር ነው።

**ሙሻ ሙሾ ስለ ስቅለቱ**
**አይንፈጉኝ ከዱቄቱ።**
**ሚሻ ምሾ፣ ሆ ሚሻ ሙሾ**
**ሳይጋገር መሸ፣**
**እሜቴ ይውጡ ይውጡ ይበሳዋል አይጡ፣**
**እሜቴ ይነሱ ፣ ይንበሳበሱ፣**
**ከቆምንበት፤ ቁንጫው ፈሳበት፣**
**ስለ አቦ፤ ያደረ ዳቦ፣ ስለ ስቅለቱ፤ ዛቅ አድርገው ከዱቄቱ»**

የበዓል ወቅት የገበያ ሥርዓቱ ከምግብ፣ ባህላዊ መጠጥ ዝግጅት አለባበስና መሰል ጉድጉዶች ጋር ተሰናኝቶ የበዓሉ ድምቀት ብቻ ሳይሆኑ ለዘመናት ትውልድን ተሻግሮ የመጣ ባህላዊ እሴት የሆነ ሀብት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን አብሮነትና ፍቅር በልዩ ሁኔታ ስፍራ አግኝተውና ከመቼውም ጊዜ በተለየ ደምቀው የሚታዩት «ፋሲካን» በመሰሉ በዓላት ወቅት ነው። የእምነቱ ተከታዮች ባይሆኑም አብሮ በመኖር በጉርብትና የፈጠሩት ህብረትና የመቻቻል ተምሳሌት ፈክቶ የሚወጣውም እንደ «ፋሲካ» በዓል ባሉት በዓላት ወቅቶች ነው።

### በፋሲካ- የሹላሌና ገጤ ጨዋታዎች

አቶ ክፍሌ ለገሰ በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ወሰን እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ላለፉት 23 ዓመታት ኖረዋል። ወደ ከተማዋ መጥተው ከባለቤታቸው ጋር መኖር ከመጀመራቸው በፊት በወጣትነታቸው የትንሳኤ በዓል በላሊበላ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በባህላዊ ሥርዓትም ጭምር ይከበር እንደነበር ያስታውሳሉ።

በበዓሉ ወቅት ከሚከናወኑት ድርጊቶች አንዱ፣ የአካባቢው ልጃገረዶች የሚጫወቱት ሹላሌ የተሰኘ ጨዋታ አንዱ መሆኑን ያስታውሳሉ። አሁንም አልፎ አልፎ ወደ ስፍራው ለቤተዘመድ ጥየቃ ሲያቀኑ ይህንን ጨዋታ እንደሚመለከቱት ይናገራሉ። እንደ አካባቢው ተወላጅ አገላለጽ፣ ሹላሌ ከትልቅ ዛፍ ላይ ጠፍር ታስሮ ልጃገረዷ በጠፍሩ ላይ ተቀምጣ የምትጫወተው ነው። ሌሎች እየገፏት እየዘፈኑ ዥዋዥዌውን ይጫወታሉ።

ግጥሙም የሚከተለውን ይዘት አለው... «ሸው ሸው ላሌ፤ እሰይ ለዓመት በዓሌ...» «ታተይ ከቋቱ ላይ ያለው እንቁላል ድመት በላው አንቺ የት ሄደሽ? እኔማ ለገብርዬ ያን እሰጥ ብዬ»፤ አግባኝ ሳልለው አግብቶኝ ነጋዴ፤ ሲያበላኝ ከረመ ነጭ ጤፍ ከስንዴ» እያሉ እንደሚጫወቱና በደስታ፤ አብሮ በመብላት፣ የተቸገረን በመርዳትና በፍፁም ሰላም ሹላሌ የተሰኘው ጨዋታ ከፋሲካ (ትንሣኤ) እስከ ዳግማይ ትንሣኤ ድረስ የሚቀጥል እንደሆነም ነግረውናል። ልጃገረዶቹ በጠፍር ላይ ሆነው መወዛወዛቸው አይሁዶች የኢየሱስ ክርስቶስን ጉዳይ በክስ አደባባይ ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ፣ ከጲላጦስ እንደገና ወደ ሄሮድስ የማመላለሳቸው ምሳሌ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በተመሳሳይ ልክ እንደ ልጃገረዶቹ ሁሉ ወጣት ወንዶችም ተመሳሳይ ጨዋታ አላቸው። የላሊበላ ወንዶች የሚጫወቱት ደግሞ የጊጤ ጨዋታ እንደሚሰኝ እኚሁ የአካባቢው ተወላጅ ይነግሩናል። ስለዚህ ጨዋታ አቶ ክፍሌ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፤ ወንዶች ቁልቋል የሚባል ተክል ቆርጠው ግንዱን መሬት ቆፍረው ይተክሉታል። ከዚያ የሾለ አንካሴ ይዘው እሱን እየወረወሩ ይወጋሉ። ውድድር አለው በተራ በተራ ያሸነፈ ይጨበጨብለታል። ረቺው በተረቺው ላይ ተፈናጦ ይሄዳል። በአንካሴ ቁልቋሉን ይወጋል። ይኸው ጨዋታ ኢየሱስ በጦር የመወጋቱ ምሳሌ መሆኑ ይነገራል።

### አክፋይና ትንሳኤ

ሌላው የፋሲካ ወይም «ትንሳኤ» በዓል ወቅት ዘርን፣ ቀለምን፣ የኢኮኖሚ ደረጃን ሳይለቅ የሚከናወን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው «አክፋይ» እየተባለ የሚታወቀው ሥርዓት የሚካሄድበትም ነው። በበዓሉ ሰሞን በተለይ ቤተሰብ የመሰረቱ ልጆች ልጆቻቸውን ይዘው አከፋይ ለወላጆቻቸው ይወስዳሉ፡፡ በዚህም አቅም የሚፈቅደውን ያህል ሙከት በግ ወይም መጠጥ ወይም ዳቦ፣ ወዘተ ወደ ቤተሰብ ይዞ በመሄድ ሲጫወቱ መዋል የተለመደ ነው፡፡

ወይዘሮ ቦጋለች ተሾመ የመርሐቤቴ ወረዳ ነዋሪ ናቸው። የዘንድሮውን የትንሳኤ በዓል ከልጆቻቸው ጋር በአዲስ አበባ ለማክበር ወስነዋል። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በሰሞነ ትንሳኤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት ያላቸው ልዩ ልዩ ሥነሥርዓቶች በኢትዮጵያውያን ዘንድ ይከናወናሉ። ከእነዚህ ውስጥ እሳቸው የሚያውቁትና በሚኖሩበት ወረዳ የሚካሄደው «የአከፋይ» ወይም አከፍለት ሥነሥርዓት ነው።

«በእኛ አካባቢ ትንሳኤን አክፋይ ይዞ ወደ ቤተሰብ በመሄድ ከሳምንት እስከ ሳምንት በደስታ እናሳልፈዋለን» የሚሉት ወይዘሮ ቦጋለች፤ ሁሉም እንዳቅሙ ወዳጅ ዘመዱን የሚጠይቅበት፣ ዝምድና የሚፈጠርበትና የሚጠናከርበትም እንደሆነ ይገልፃሉ።

በተለይ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ልጆች ሲወለዱ «ክርስት አባትና እናት» በሚል ለቅርብ ወዳጅ የሚሰጡ መሆኑን አስታውሰው በዋናነት የክርስትና ልጅ የክርስትና አባት/እናቱን እቤቱ በመሄድ የሚጠይቅበትና እንኳን አደረሰህ የሚባባልበት መሆኑን ይገለፃሉ። በምላሹ የክርስትና አባት/እናት ልጆቻቸው በትንሳኤ ሰሞን ለጥየቃ ቤታቸው ሲመጡ ስጦታ እንደሚያዘጋጁ ይናገራሉ። ይህ ባህላዊ ሥርዓት በደም የማይተሳሰር ወዳጅን ዘመድ የማድረጊያ አንዱ መንገድ መሆኑንም ጠቅሰው፣ የትንሳኤ በዓልን መሠረት አድርጎ የሚከናወን መሆኑን ነግረውናል።

### ኢትዮጵያዊ እሴቶች

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የፎክሎርና የአትሮፖሎጂ ክፍል እንደሰነደው በሰሜን ሸዋ ምንጃር አካባቢ ደግሞ የበዓሉ አከባበር በዕለተ ሐሙስ ይጀመራል፤ ይህ ዕለት ጉልባን፣ ዳቦና ጠላ ተዘጋጅቶ በመብላትና በመጠጣት ይታለፋል። በማግስቱ ደግሞ የስቅለት ወይም የስግደት ዕለት በዋናነት የአካባቢው ሽማግሌዎችና አዛውንቶች በመስገድ የሚሳተፉበት ዕለት ነው። ቅዳም ስዑር (የቅዳሜ ስዑር ዕለት) ማታ ዶሮ ይታረዳል። የዶሮ ወጥ የጾም መፍቺያ በመሆኑ የሚበላው ሌሊት ዶሮ ሲጮህ ሲሆን፣ በዚህ ሰዓት ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ የቤተሰብ አባላት ከእንቅልፉ ተቀስቅሶ እንዲገድፍ ወይም ጾሙን እንዲፈታ በማድረግ ይሆናል።

በደቡብ ክልል ሸካ ዞን የሚገኙት ሸከቾዎችም ፋሲካን በራሳቸው ባህላዊ መለያ ያከብሩታል። በዓሉ ሐሙስ የሚጀምር ሲሆን ዕለቱ «ዳጺ ማዮ ማዮ» ይባላል። ይህም የንፍሮ ቀን ማለት ሲሆን፣ ቀኑን በጾም በማሳለፍ ወደማታ የሚበላው ምግብ ንፍሮ ብቻ ነው። በሌሎች ቦታዎችም በጸሎተ ሐሙስም ጿሚዎቹ ጉልባንና ንፍሮ ቀምሰው እስከ ትንሣኤ ሌሊት ሳይመገቡ ያከፍላሉ። ባቄላ፣ ስንዴና ጥራጥሬ ተቀላቅሎበት የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ጉልባን ነው። ዓርብ ስቅለት ከስግደት መልስም ጉልባን ይበላል፡፡ የኀዘን መግለጫ ሆኖ የተወከለ ነው።

### ሚሻ ሚሾ-የፋሲካ ጨዋታ

በፋሲካ ወቅት ከሚከበሩ ባህላዊ ሥርዓቶች መካከል በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የምናገኘው «የሚሻ ሚሾ» በዓል ሌላው ባህላዊ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ልዩ ልዩ መገለጫዎች እና ትርጉሞች አሉት፡፡ ይህንንም በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ እውቀት ያላቸው ምሁራን በመጽሐፋቸው ላይ ያሰፈሩትን ዳሰሳ ተመልክተን ይበልጥ ለመረዳት እንሞክር።

የፋሲካ በዓል ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዳግማይ ትንሣኤ እየተከበረ ይቆያል። የበዓሉ መንደርደርያ ጸሎተ ሐሙስ ሆኖ ማዕከሉን በተለይ በዓለ ስቅለትን ያደርጋል። ከበዓለ ስቅለት ባህላዊ መገለጫዎች አንዱ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚዘወተረው «ሚሻ ሙሾ» ነው። ይህንንም ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓት ቀሲስ ሰሎሞን ወንድሙ መታፈሪያ «መዝገበ በረከት ዘሰሙን ቅድስት» በተሰኘውና ለንባብ በበቃው መጽሐፋቸው ዘርዘር አድርገው ማስረጃዎች እያጣቀሱ አቅርበውታል።

ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ወንዶች ሕፃናት «ሚሻ ሚሾ» እያሉ እየዘመሩ በየቤቱ እየዞሩ ዱቄት ይለምናሉ። በዓሉ በባህላዊ ሥርዓቱ በቂጣ ስለሚከበር የአይሁድ የቂጣ በዓልን ይመስላል። አለቃ ታየ ገብረ ማርያም በ1902 ዓ.ም በታተመው የትብብር ሥራቸው «ሚሻ ሚሾ» የሚለው ስያሜ የት መጣንም «ውሾ ውሾ» ከሚል እንደሆነ ያስረዳሉ።

ሕፃናት ከሐሙስ ጀምረው እስከ በዓለ ስቅለት ምሽት የሚሻ ሙሾን ዝማሬ እያሰሙ በየቤቱ በመዞር ዱቄት የሚያሰባስቡት ትውፊታዊ ክዋኔ አላቸው። ሕፃናቱ በየቤቱ ዱቄት ለመሰብሰብ ሲዞሩ በቀለማት ወይም በእሳት ተለብልቦ የተዥጎረጎረ ቀጭን ዘንግ ይይዛሉ። መሬቱን በዘንግ በመምታት ዱቄት እስኪሰጣቸው ድረስ በተለያዩ ግጥሞች የታጀበ ዝማሬ ያሰማሉ። ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘንግ መመታቱን ለመዘከር ነው። በዝማሬያቸውም...

**ሙሻ ሙሾ ስለ ስቅለቱ**
**አይንፈጉኝ ከዱቄቱ።**
**ሚሻ ምሾ፣ ሆ ሚሻ ሙሾ**
**ሳይጋገር መሸ፣**
**እሜቴ ይውጡ ይውጡ ይበሳዋል አይጡ፣**
**እሜቴ ይነሱ ፣ ይንበሳበሱ፣**
**ከቆምንበት፤ ቁንጫው ፈሳበት፣**
**ስለ አቦ፤ ያደረ ዳቦ፣ ስለ ስቅለቱ፤ ዛቅ አድርገው ከዱቄቱ»** በማለት ይዘምራሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን በርካታ ግጥሞችና የጨዋታ ዓይነቶችም እያዜሙ በዓሉን ታዳጊዎቹ ያከብሩታል። እኛም መልካም በዓል እንላለን፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ጀግና በየዘርፉ

ዋለልኝ አየለ

ዛሬ ዕለቱ ፋሲካ(ትንሳኤ) ነው። የትንሳኤ በዓል ዕለቱን(እሁድ) አይለቅም እንጂ ቀኑ ይቀያየራል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ወሩን ሁሉ ሊለቅ ይችላል። ስለዚህ ሳምንቱ በታሪክን ስናስታውስ የሳምንቱ ክስተቶች የፋሲካ ሰሞን ክስተቶች ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ ለማለት ነው።

በዚህ ሳምንት እጅግ ግዙፍና በርካታ የታሪክ ክስተቶች ተከናውነዋል። ጥቂቶችን እናስታውስና አንዳንዶቹን ዘርዘር አድርገን እናያለን።

ከ11 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም አረፉ።

ከ155 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዝያ 3 ቀን 1860 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ታማኝ የጦር መሪ የነበሩት ፊታውራሪ ገብረሕይወት ጎሹ (ገብርዬ) አረፉ።

ከ113 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዝያ 3 ቀን 1903 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ታማኝ መኳንንት መካከል አንዱ የነበሩት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው (አባ ቀማው) አረፉ።

ከአንድ ሺህ 510 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዝያ 5 ቀን 505 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ርዕሰ ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድ ማህሌታይ ተወለደ። በዚህ ሳምንት እና በዚሁ ቀን ከ162 ዓመታት በፊት ሚያዝያ 5 ቀን 1853 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ልጅ የሆነው «ባይተዋሩ መስፍን» ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ተወለደ።

አሁንም በዚሁ ሳምንትና ቀን ከ73 ዓመታት በፊት ሚያዝያ 5 ቀን 1942 ዓ. ም ፀረ ፋሽስቱ አርበኛ ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ አረፉ።

ከ155 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ዘመነ መሳፍንትን አንኮታኩቶ በመጣል ኢትዮጵያን አንድ ያደረጉት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ አረፉ።

ከ72 ዓመታት በፊት በዛሬዋ ቀን ሚያዝያ 8 ቀን 1943 ዓ.ም የ«ቃኘው» ሻለቃ ሰላም አስከባሪ ኃይል ወደ ኮሪያ ለመዝመት ከጅቡቲ ወደብ ተንቀሳቀሰ።

እነዚህ ክስተቶች በተለያዩ ዘመናት በዚህ ሳምንት የተከሰቱ ናቸው። የአንዳንዶቹ በተለያየ አጋጣሚ ብዙ የተባለለት ሲሆን የአንዳንዶቹ ግን ብዙም ያልተባለለት ነው። ስለዚህ የጀግንነታቸውን ያህል ብዙም አልተዘመረላቸውም ያልናቸውን ዘርዘር አድርገን እናስታውሳቸው።

### ገብርዬ

ትውልዳቸው ጋይንት የሆነው ፊታውራሪ ገብርዬ ሙሉ ስማቸው ገብረሕይወት ጎሹ ነው። በጀግንነታቸውና በጦር አመራራቸው እጅግ የተደነቁ ጀግና ነበሩ። ለዚህም ነው ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ «ይዋጓል እንደ ገብርዬ፤ ይማሯል እንደ አካልዬ» ብለው የተናገሩት። «አካልዬ» ያሏቸው «ባለአራት ዓይን» የሚባሉትን ሊቀ ሊቃውንት አካለወልድ ሰርፀወልድን ነው።


ገብርዬ ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የሽፍትነት ጊዜ ጀምሮ ታማኝ አጋራቸው ነበሩ። ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻው ዘመናቸው ብዙ ሠራዊታቸው እየከዳቸው የወታደራቸው ቁጥር እጅግ ተመናምኖ ነበር።

32 ሺህ ዘመናዊ የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱን ሊወጋ ዝግጅት ሲያደርግ ፊታውራሪ ገብርዬ 5000 ጦር ብቻ ይዘው እንዲገጥሙ ታዘዙ። ሚያዝያ 3 ቀን 1860 ዓ.ም በዕለተ ዓርብ፣ በስቅለት ቀን እሮጌ ሜዳ ላይ እየተዋጉ ሳለ ሞቱ።

ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስም የረጅም ጊዜ ታማኝ አጋራቸውንና ጀግና የጦር መሪያቸውን አጡ። ሞታቸውን ሲሰሙም «የእናቴ ልጅ ጓዴ» ብለው አለቀሱ። ከሦስት ቀናት በኋላም (ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም) ዳግማዊ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ገብርዬን ተከተሏቸው።

### ራስ ተሰማ ናደው

ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ.ም የዙፋናቸው ወራሽ ልጅ ኢያሱ ሚካኤል እንደሆነ ሲያሳውቁ ራስ ተሰማ ናደውን ሞግዚትና እንደራሴ አድርገው ሾሟቸው። ከጥቂት ጊዜያት በኋላም ሐምሌ 18 ቀን 1901 ዓ.ም ለራስ ተሰማ ናደው «ራስ ቢትወደድ» የሚል ማዕረግ ተጨመረላቸው።



ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ

ራስ ተሰማ ናደው በንጉሥ ምኒልክ አገር የማቅናት ዘመቻ ወቅት ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረከቱ ሰው ናቸው። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ እንደፃፉት፣ ራስ ተሰማ ከኢሉባቦር ጀምሮ እስከ ነጭ ዓባይ ድረስ ያለውን ግዛት አቅንተዋል። በዓድዋ ጦርነት ወቅትም ትልቅ የጀግንነት ታሪክ ፈፅመዋል።

ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በሕመም ምክንያት ሥራቸውን ማከናወን ባለመቻላቸው የሥልጣን ሽሚያው የከረረ ሆኖ ነበር። እቴጌ ጣይቱ ብጡል የባለቤታቸውን ሥልጣን በመጠቀም አድራጊ ፈጣሪ መሆን ሲጀምሩ እቴጌይቱ ከመንግሥት የፖለቲካ ሥራ እንዲገለሉ ካደረጉት መኳንንት መካከል ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው ዋናው ነበሩ።

ልጅ ኢያሱ በአያታቸው ዙፋን ተቀምጠው አገር የማስተዳደሩን ሥራ በጀመሩበት ወቅት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው ከጎናቸው ሆነው የእንደራሴነቱንና የማማከሩን ሥራ ያከናውኑ ነበር።

ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው በንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ታማኝ የነበሩና ከደጃዝማችነት ተነስተው ራስ ቢትወድ ማዕረግ ላይ የደረሱ ሰው ነበሩ።

የልጅ ኢያሱ ሚካኤል እንደራሴ ሆነው «ራስ ቢትወደድ» ከተባሉ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ሚያዝያ 3 ቀን 1903 ዓ.ም በድንገት አርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈፅሟል። የሞታቸው ምክንያት ከሐሜት ያለፈ የጠራ መረጃ የለውም።

### ቅዱስ ያሬድ

ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ርዕሰ ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድ ማህሌታይ የተወለደው ከ1510 ዓመታት በፊት ሚያዝያ 5 ቀን 505 ዓ.ም ነበር።

ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ አብዩድ (ይስሃቅ) እና ከእናቱ ተውክልያ (ክርስቲና) ታላቋ አክሱም ከተማ ውስጥ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ከአጎቱ ከአባ ጌዴዎን ዘንድ ትምህርት ሊማር ቢሔድም ለበርካታ ዓመታት ትምህርት ሊገባው አልቻለም ነበር። በዚህም የተነሳ መምህሩ ይገርፉትና ይገሥፁት ነበር። እርሱም ከትምህርቱ ክብደት ባለፈ የመምህሩ ተግሣፅ ሲበረታበት ጊዜ ከአባ ጌዴዎን ቤት ወጥቶ በመሸሽ ላይ ሳለ ደክሞት ከአንድ ዛፍ ሥር ተቀመጠ።

ከዛፉ ሥር ተጠልሎ ሳለ አንዲት ትል ፍሬውን ለመመገብ ወደ ዛፉ ስትወጣ፤ ነገር ግን መውጣት ስለተሳናት በተደጋጋሚ ስትወድቅ ቆይታ ከብዙ ሙከራ በኋላ ከዛፉ ላይ ወጥታ ፍሬውንም ስትመገብ ይመለከታል። ቅዱስ ያሬድ የትሏን ትጋት ካየ በኋላ እርሱም በተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርግ የከበደው ምሥጢር እንደሚገለጽለት በማመን ወደ መምህሩ ተመልሶ ይቅርታ በመጠየቅ ትምህርቱን እንደገና መቀጠል ጀመረ።

እግዚአብሔርን በጸሎት እየተማጸነ ትምህርቱን



ራስ ተሰማ ናደው

ሲከታተል ከቆየ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ልቡናው ብሩህ ሆኖለት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜን አጠናቆ መዓርገ ዲቁና ተቀበለ። ከመምህሩ ከአባ ጌዴዎን በተማረው መሠረት የእብራይስጥና የግሪክ ቋንቋዎችን ደህና አድርጎ ያውቅ ነበር ይባላል።

በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ከዓመት እስከ ዓመት ድረስ በየክፍለ ዘመኑ በክረምትና በበጋ፣ በመጸውና በጸደይ፣ በአጽዋማትና በሰንበታት፣ እንዲሁም በመላእክት፣ በጻድቃን፣ በሰማዕታት፣ በደናግል በዓላት የሚደረስ ቃለ እግዚአብሔር በሦስት ዜማዎች ማለትም በግእዝ፣ በዕዝልና በአራራይ ደረሰ። የሰው ንግግር፣ የአዕዋፍ፣ የእንስሳትና የአራዊት ጩኸት ሁሉ ከነዚህ ከሦስቱ ዜማዎች እንደማይወጡ መጽሐፈ ስንክሳር ይናገራል።

ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መሥዋዕትና ምዕራፍ በቅዱስ ያሬድ የተደረሱ የዜማ መጻሕፍት ናቸው። በአንዲት ዕለት ቅዱስ ያሬድ ከብሉይና ከሐዲስ፣ እንደዚሁም ከሊቃውንትና ከመነኮሳት የተውጣጣውን መንፈሳዊ ድርሰቱን በዘመኑ ከነበረው ንጉሥ ከአፄ ገብረ መስቀል ፊት ቆሞ ሲዘምር ንጉሡ በድምፁ በመማረኩ የተነሣ ልቡናው በተመስጦ ተሠውሮበት (የሚያደርገውን ባለማወቁ) የቅዱስ ያሬድን እግር በጦር ወጋው። ከቅዱስ ያሬድ እግር ደምና ውኃ ቢፈስስም ነገር ግን ማኅሌቱን እስኪፈጽም ድረስ ሕመሙ አልተሰማውም ነበር።

ንጉሡም ያደረገውን ሁሉ ባወቀ ጊዜ ደነገጠ፤ ጦሩንም ከእግሩ ነቅሎ «ስለፈሰሰው ደምህ ዋጋ የምትፈልገውን ሁሉ ለምነኝ» እያለ ተማጸነው። ቅዱስ ያሬድም «ላትከለክለኝ ማልልኝ» ብሎ ቃል ካስገባው በኋላ፣ ወደ ገዳም ሔዶ ይመነኩስ ዘንድ እንዲፈቅድለትና እንዲያሰናብተው ለመነው። ንጉሡም ከመኳንንቱ ጋር እጅግ አዘነ፤ ተከዘ። ከእርሱ እንዲለይ ባይፈልግም ነገር ግን መሐላውን ማፍረስ ስለከበደው እያዘነ አሰናበተው።

ከዚያም ቅዱስ ያሬድ በአክሱም ጽዮን ቤተ መቅደስ በታቦተ ጽዮን ፊት ቆሞ «ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን መዐርገ ሕይወት ... ፈጽሞ የከበርሽና የተመሰገንሽ፣ ከፍ ከፍም ያልሽ፣ የብርሃን መውጫ የሕይወት ማዕረግ የሆንሽ» እያለ አንቀጸ ብርሃን የተባለውን የእመቤታችንን ምስጋና እስከ መጨረሻው ድረስ ደረሰ።

ከዚህ በኋላ ከአክሱም በስተደቡብ አቅጣጫ ሄዶ በሰሜን ተራሮች አካባቢ በጾም በጸሎት ተወስኖ ሥጋውን እጅግ እያደከመ ኖሮ ገድሉን በዚያው ፈጸመ። እግዚአብሔርም ስሙን ለሚጠራ፣ መታሰቢያውን ለሚያደርግ ቃል ኪዳን ሰጠው።

ርዕሰ ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድ ማህሌታይ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ልዩና ብቸኛ የሚያደርጓትን ሀብቶች(መለያዎች) ባለቤት ያደረገ ታላቅ ሊቅ ነው።

### ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ

ፀረ ፋሽስት አርበኛው ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ የተወለዱት ግንቦት 13 ቀን 1884 ዓ.ም ጎጃም ውስጥ፣ ሜጫ፣ ጉታ አውራጃ አካባቢ ነው። አባታቸው ደጃዝማች ጀምበሬ እምሩ የሜጫ፣ የዴንሳ፣ የጉታና የአገው ምድር ባላባት በመሆን ለብዙ ዓመታት አካባቢውን አስተዳድረዋል። ደጃዝማች ጀምበሬን ጨምሮ አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው ሁሉ የደጃዝማች ማዕረግ ነበራቸው። መንገሻ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ብልህና አስተዋይ እንዲሁም በአልሞ ተኳሽነታቸው ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው፤ በበገና ድርደራ እና በፈረስ ግልቢያም የሚታወቁ ነበሩ። ለአደንና ለውሃ ዋናም ልዩ ፍቅር ያላቸው ጀግና ነበሩ። በተለያየ የጀግንነት ተሳትፎ ውስጥ ያለፉት መንገሻ በ32 ዓመታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ በማግኘታቸው የቡሬ ዳሞት አውራጃንና የሰከላ አካባቢዎችን ማስተዳደር ጀመሩ።

የተለያዩ አስተዳደራዊ ሥራዎችን እየሠሩ በ1928 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ወረረ። ደጃዝማች መንገሻ በግዛታቸው ማለትም በሜጫ አውራጃ አካባቢ የሚገኘውን ጦር አስከትለው ከራስ እምሩ ጋር በትግራይ በኩል በመዝመት ለአገራቸው በጀግንነት ተዋጉ። ከማይጨው ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞችም ወደ ኋላ በማፈግፈግና እንደገና በየአካባቢው የሚገኘውን የጎበዝ አለቃ እያስተባበሩ ጠንካራ ውጊያ ለማድረግ ሲዘጋጁ ደጃዝማች መንገሻም የአገው ምድር፣ ሠከላ፣ ሜጫ፣ ጉታ፣ አቸፈር፣ አለፋ ጣቁሳ አካባቢ አርበኞችን በማስተባበር ከወራሪው ጋር መፋለም ጀመሩ።

በ1929 ዓ.ም የመጀመሪያ ወር ላይ የጎንደርና የጎጃም አካባቢ የፋሺስት ጦር የበላይ አዛዥ የደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬን መጠናከርና በየአካባቢው የጦር አለቆችን መመደባቸውን ሲሰማ እጅግ ደነገጠ። ይህን የአርበኞችን መጠናከር ሊቋቋምልኝ ይችላል ብሎ ያሰበውን የጦር አዛዥ ሹም ሽር በማድረግና በርካታ ሰራዊት በመመደብ ጦሩ በከተሞች ተወስኖ ምሽግ ይዞ፣ ኃይሉን አጠናክሮ እንዲከላከል አዘዘ።

ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ቢቸናን፣ ራስ ኃይሉ ደብረ ማርቆስንና ሞጣን እንዲሁም ራስ በዛብህ ደግሞ ዳሞት አካባቢን በማካለል የጠላትን ጦር እረፍት ነሱት። ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ከደጃዝማች በላይ ዘለቀና ከሌሎች የውስጥ አርበኞች ጋር በመሆን በከፍተኛ መናበብና መቀናጀት እየተፋለሙ ቀጠሉ።

ደጃዝማች መንገሻ አስደናቂ የጦርና የደህንነት መረጃ አመራር ችሎታም ነበራቸው። የጠላትን እንቅስቃሴ ከውስጥ የሚያወጡና ከውጭ የሚጠቁሙ የመረጃ ሰዎች የሚገናኙባቸው ምስጢራዊ የግንኙነት መዋቅር ዘርግተውም ከመሪ አርበኞች ጋር ይገናኙ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም «ጉታ ገበርማ» በተባለው ቦታ ከጠላት እጅ የተማረኩ መገናኛዎችንና የመልዕክት ማስተላለፊያ መስመሮችን አገናኝተው አቶ ጊላ ወልደ ጊዮርጊስ (በኋላ ደጃዝማች ) በሚባል ብልህ ሰው የሚመራ የስለላና የፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ አቋቁመው ነበር፡። በነዚህ የመገናኛ መሣሪያዎችም የጠላትን እንቅስቃሴ ማዳመጥና የጠላትን የምልክት መገናኛ ኮዶችን መጥለፍ ተችሎ ነበር።

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያውያን አርበኞች ትግል ከፉኛ ተዳክሞ በነበረበት ወቅት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከሱዳን ተነስተው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ እንደጀመሩ የጠላት ኃይል በቡሬ ከተማ በተጠናከረ ሁኔታ ምሽግ ሠርቶ ጠበቃቸው። ይህ የጠላት ኃይል መወገድ ነበረበትና ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ ከዳሞቱ መስፍን ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጋር ተቀናጅተው በማጥቃት የጠላት ጦር ቡሬን ለቅቆ እንዲወጣ አደረጉት። በመቀጠልም የፋሺስት ኃይል ሙሉ ጎጃምን ለቅቆ ለመውጣት ተገደደ። ንጉሰ ነገሥቱም በደብረ ማርቆስ በኩል አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ።

ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬም በቢትወደድነት ማዕረግ በጎጃም እንደራሴነት በማገልገል ላይ ሳሉ በ1937 ዓ.ም ወደ ሸዋ፣ አዲስ አበባ ተዛውረው በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት እንደራሴነት እስከ 1938 ዓ.ም ድረስ ካገለገሉ በኋላ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ።

ደጃዝማች ቢትወደድ መንገሻ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው በማገልገል ላይ ሳሉ በሰሜኑ ግንባር በሸሬው ጦርነት በቦንብ ፍንጣሪ የቆሰለው አካላቸው ቁስሉ እያመረቀዘ ሲያሰቃያቸዉ ቆይቶ በእረፍት እጦት ምክንያት በቂ ህክምና ባለማግኘታቸው በ1942 ዓ.ም አረፉ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በከፍተኛ ክብር በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስተ ማርያም ካቴድራል ተፈፅሟል።

# የዝነኞች ገጽ

# ሚሻሚሾና ታደሰ አለሙ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**ታደሰ አለሙና ፋሲካ በሚገርም መልኩ ተቆራኝተዋል።ምን አቆራኛቸው ከተባለ ደግሞ ሙዚቃ፣ ከሙዚቃም ደግሞ የማይረሳና የማይዘነጋ ትዝታና የጥበብ ጥላ ያረፈበት ሚሻሚሾ የተሰኘ ሙዚቃ ነው።ሚሻሚሾ በጥኡም ቃና የተጠመቀም የፋሲካ በአል ማድመቂያ የተከሸነ ወይን ነው ቢባል አልተጋነነም።የትንሳኤ በአልና ድምፃዊ ታደሰ የተቆራኙበት ገመድም ከአመት አመት ሳይበጠስ ወርቃማና ፈርጣማ በሆነ የጥበብ ሰንሰለት ተሳስረው በየፋሲካው ሁሌም አዲስ ሆነው ይመጣሉ።**



በፋሲካ በአል ሚሻሚሾ ሁሌም በአዲስ ቃና ይደመጣል። በየበአላቱ አዳዲስም ሆነ ቆየት ያሉ ሙዚቃዎችን መስማት የተለመደ ነው። ነገር ግን እንደዚህ ሙዚቃ ከበአል ጋር መሶብ ከነአፎቱ መስሎ የተሰካካ ሙዚቃ ፈልጎ ማግኘት በጨረቃ ብርሃን ከመሬት ላይ ጤፍ እንደመልቀም ይቆጠራል። በሚሻሚሾ ሙዚቃው ውስጥ ባህልና ሃይማኖት በሚገርም መልኩ ተዋህደዋል።ፋሲካ ሃይማኖታዊ በአል ቢሆንም፣ በበአሉ ያሉትን ሃይማኖታዊ ይዘቶች ከኢትዮጵያ የባህል ቅኝት ጋር ደህና አድርጎ በመከሸን ሁለቱ ያላቸውን ትስስር አጉልቶ ለማውጣት ተችሎታል።ሚሻሚሾ ድምጻዊው ስለበአል የሰራው የመጀመሪያ ሰራው አይደለም።ከዚያ ቀደም "አውዳመት" የሚል ሌላ ሥራም ነበረው፤ ይሁን እንጂ ሙዚቃው እንደአብዛኛዎቹ የበአል ሙዚቃዎች በአሉን ከማድመቅ ባለፈ የተለየ የትርጉም ይዘት አልነበረውም።ሚሻሚሾ የተሰኘው ሙዚቃ ተወዳጅ እንዲሆንና ድምጻዊውም ገኖ እንዲወጣ ያደረገው ነገር ቢኖር በዜማና ግጥም ታሽተው ከጆሮ ቁልቁል የሚፈሱት የታሪክ ፍሰቶች ናቸው።

ለመሆኑ ሚሻሚሾ ሲባል ምን ማለት ይሆን? ትርጓሜው ከስቃይ፣ ከመከራና ከብዙ ችግር በኋላ የሚገኝ ደስታ እንደማለት ነው።በአገው አካባቢ የሚዘወተር ባህላዊ የወጣቶች ጨዋታም ነው።ይህን ሙዚቃ እንድንወደውና እንድናደንቀው የሚያደርገን አንደኛው ምክንያት እዚህ ጋር ይገናኛል፡፡

ታደሰ ይህንን ባህላዊ ጨዋታ መነሻ በማድረግ ጥበባዊ ለዛ በፈሰሰበት መልኩ የፋሲካን ክዋኔዎችና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በመቀላቀል ለጆሮ ጥኡምና ማራኪ እንዲሆን አድርጎታል።በበአለ ሥርዓቱ ውስጥ በፋሲካው ሰሞን ያሉትን በልዩነት የሚከበሩትን ዕለታት በመጥቀስም ያላቸውን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ ያስመለክተናል።ካነሳነው አይቀርም የሚሻሚሾ ሙዚቃ ግጥም እንዲሁም በበአልና ባህል መሃከል የተሰደሩበትን መንገድ እንቃኛቸው፡፡

ገጥምና ዜማውን በደፈናው ስንመለከት በሙዚቃው የመጀመሪያ ምዕራፍ ወይንም "በቀራኒዮ ላይ ታየ" የጌታችን የመድኃኒታችን የእየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሳኤን ይተርካል።ያሳለፋቸውን መከራና ስቃይ በሙሉ ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን እንደጠበቁ ተቀምጠዋል።በስተመጨረሻም ስቃይና ሞትን ድል አድርጎ ሲነሳ የሙዚቃው ዳራም እንዲሁ ይቀየራል።ከረሃብና ጥም ወደ ጥጋብና በረከት፣ ከኀዘንና መከራ ወደ ደስታና ፍሰሃ ሲሸጋገር ሙዚቃው የተገነባበት ግጥምና ዜማም ግሩም በሆነ የሽግግር ሂደት እንዲሁ መሰረቱን ቀይሮ ከባህላዊው ጨዋታ ጋር ያዋዛዋል።ከእየሩሳሌም ወደ አገው ምድር የተደረገ የተሳካለት ምናባዊ ጉዞ!

በሙዚቃ ሥራው ላይ እንደምንመለከተው የሙዚቃ ስልቱ በብዛት በአገው አካባቢ የሚዘወተር ሲሆን ከአሸንዳ ጭፈራ ጋርም የሚያመሳስል ነገር አለው። እስቲ ይህን ሙዚቃ ለሁለት ከፍለን እንመለከተው። የመጀመሪያው

**በቀራኒዮ ላይ ታየ**
**ታየ ታየ**
**በጎልጎታ ላይ ታየ**
**ታየ ታዬ**
**የዓለም መድኃኒት የጌታ ትንሳኤ**
**የጌታ ትንሳኤ**
**በስተ ፋሲካ በጌታ ትንሳኤ**
**በጌታ ትንሳኤ**
..........
አርባ ቀን አርባ መአልት ገዳመ ቆሮንጦስ ጌታ ተፈትኖ
ለፈጠረው ፍጡር ተወግሮ ተሰቅሎ የዓለም ቤዛ ሆኖ
ክርስቶስ ታጅቦ እየበተኑለት የዘንባባ ለምለም
ሆሳዕና በአርያም በአህያ ውርንጫ ገባ እየሩሳሌም
ከደቀ መዝሙራት በ30 ዲናር ይሁዳ ሸጦት
በፀሎተ ሐሙስ ስጋ ደሙን ሰጠን ለኛ ድህነት
........

በእነዚህ ግጥሞች ውስጥ ፈጣሪ የሰውን ልጅ ወዶ በሰው ልጆች ሀጢያት ምክንያት የከፈለውን ታላቅ መስዋዕትነት እያነሳ ይዘክራል። በስቅለቱ ዋዜማ የነበረውንም ሁኔታ ከታላቁ መጽሐፍ እየቀነጨበ ስዕላዊና ገላጭ በሆነ መልኩ ይተርከዋል። እንገዲህ በአንዲት የስድስት ደቂቃዎች ገደማ ርዝመት ባላት የሙዚቃ ሥራ ውስጥ ይህንን የሚያህል ግዙፍ ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ከማሳየቱም ባሻገር ግጥምና ዜማው ከድምጹ ጋር ተዋህዶ የቀረበበት መንገድ የታደሰ አለሙን የሙዚቃ ጥበብ የሚያንጸባርቅም ጭምር ነው። በዚህ የታደሰ አለሙ ዘመን አይሽሬ ሙዚቃ ውስጥ ከላይ ለማሳየት ከሞከርነው ግጥምና ዜማ ቀጥሎ የሙዚቃው የጀርባ አጥንት የሆነው ሁለተኛውና በማበቂያው ላይ የምናገኘው የመጨረሻው ክፍል ነው። መጠሪያውም የተቀዳው ከዚሁ ክፍል ነው። የዜማ ቅኝቱን ለወጥ በማድረግም ኦ ሚሻሚሾ ሲል ስሜትን ቀስቀስ በሚያደርግ መልኩ ይጀምረዋል።

**ኦ ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ከብረሽ ቆይኝ ከብረሃ በ30 ጠምደሃ**
**ከብረሽ ቆይኝ ከብረሽ በ30 ጠምደሽ**
**የጌታዬ ሰቀላ ተሸልሟል በአለላ**
**የእመቤቴ አዳራሽ ተሸልሟል በሻሽ**
**ኦ ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**እምዬ ይነሱ ይንበሳበሱ**
**እማ ከድፎው ቢሰጡኝ ቢቆርሰው**
**እማ ከጉልባኑ ይዝገኑ ይዝገኑ**
**እማ ከዱቄቱ ትንሽ በወጭቱ**
**ማጣፈጫ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**መሰልቀጫ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ትንሽ ቅቤ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ለወገቤ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ትንሽ ጨው**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ቆንጥረው**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ከቅመሙም**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ጣል አርገው**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**በርበሬውን**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ቀላቅለው**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**ማጣፈጫ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**
**መሰልቀጫ**
**ሚሻሚሾ ሚሻሚሾ**

ሙዚቃውን አስተውለን ከተመለከትነው አብዛኛውን ባህል ነክ የሆኑ ሃሳቦችና የባህል ጭፈራ ስልትን እናገኝበታለን። የሥነ ግጥም ቅኝቱም ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ እናቶች ጓዳ የተቀዳ ስለመሆኑ ነጋሪ አያሻውም። እማ ከድፎው...እማ ከጉልባኑ..ትንሽ በውጭቱ...ትንሽ ቅቤ..መሰልቀጫ..ለወገቤ..ከቅመሙ.. ማጣፈጫ..ጣል አድርገው...እያለ ጣል ያደረጋቸው የዜማው ማጣፈጫዎች በእጅጉ የተዋቡ ቃላቶች ናቸው። የማህበረሰባችን ባህልና በአላዊ ትውፊቶች ምን ያህል ከሃይማኖት ሥርዓት ጋር የተቆራኙ እንደሆኑ ያመላክተናል።

በበአለ ፋሲካው የተከናወኑትን ሁነቶች የሚዳስስና የሚገልፅ ነው።ክርስቶስ በአህያ ውርንጭላ ላይ ሆኖ ወደ እየሩሳሌም መሄዱን ፣ በሃዋርያው ይሁዳ በ 30 ዲናር መሸጡን ፣ በዕለተ ሐሙስ ወይንም ደግሞ በፀሎተ ሐሙስ ይህ "ነገ የሚፈሰው ደሜ ነው...ይህም ነገ የሚቆረሰው ስጋዬ ነው" በማለት ክርስቶስ የተናገረውን ቃል በመጽሐፉ ፣ እንደተጻፈው ከዚህ በሚስማማ መልኩ ታደሰም ..... በፀሎተ ሐሙስ ስጋ ደሙን ሰጠን ለኛ ድህነት...በማለት ገልጾታል። ከዕለተ ስቅለቱ ከአርብ እስከ ዕለተ ትንሳኤው እሁድ ድረስ ያሉትን ሃይማኖታዊ እውነታዎች በመግለጽ "እንኳን ደስ አላችሁ ሞትን ድል አድርጎ"፤ የጌታችን ሞትን ድል አድርጎ የመነሳትን ብስራት እያበሰረን ይጨርሳል። እንግዲህ ድምጻዊው ለፋሲካችን ማደመቂያ ይሆን ዘንድ ያበረከተልን ይህ ውብ ሙዚቃ እንደሙዚቃነቱ ብቻ አድምጠነው የምናልፍ ከሆነ ተሳስተናል። ሙዚቃውን አድምጠንና መርምረን አጭቆ የያዘውን ሌላኛውን የሙዚቃውን ወበት ከአዕምሮአችን እንዲሁም ከልባችን ልናኖረው ይገባል። በነገራችን ላይ በዚህ የሙዚቃ ሥራ ውስጥ ሁለት የተለያዩ የዜማ ቅኝቶች እንዳሉ መርሳት የለብንም። እነዚህ ሁለት ዜማዎች አንደኛው የድምጻዊው ታደሰ አለሙ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሕዝብ ዜማ ነው። በዚህ የሕዝብ ዜማ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ግጥሞችም በድሮው ጊዜ እንደባህላዊ ባሉ ጨዋታዎች መሀል የሚዘወተሩ ናቸው። ድምጻዊው ልናደንቀው የሚገባው ሁለተኛው ምክንያትም የቀደመውን ቱባ ባህል በሚያምር መልኩ ስላሳየን እንዲሁም ስላስተዋወቀንም ጭምር ነው።

**እንግዲህ ድምጻዊው ለፋሲካችን ማደመቂያ ይሆን ዘንድ ያበረከተልን ይህ ውብ ሙዚቃ እንደሙዚቃነቱ ብቻ አድምጠነው የምናልፍ ከሆነ ተሳስተናል**

ከዚህ የአውዳመት ስጦታ ባሻገር ታደሰ አለሙ በብዛት የሚታወቀበት ሌላም ልዩ መታወቂያ አለው።መቼም ይህንን ልዩ ስጦታውን በወግ ማዕረግ ተጋብቶ ወዳጅ፣ ቤተዘመዱን ጠርቶ የተጨፈረላቸው ሙሽሮችም ሆኑ የጨፈሩ አጃቢና ሚዜዎች በደንብ ያስታውሱታል።ያለእርሱ ሙዚቃዎች ሠርጉም ሠርግ፣ ድግሱም ድግስ አይመስልም።ከእያንዳንዱ ሠርግ ቤት የሚወጣው ይህ የሙዚቃ ቃና በልዩ ጸአዳ የተከሸነ ልዩ መአዛ አለው።ከበስተጀርባው ደግሞ ታደሰ አለሙ አለ።

የሰሞንኛውን የፋሲካ በአል ሙዚቃን ጨምሮ በርካታ የሠርግና የባህል ማራኪ የሙዚቃ ሥራዎችን ዘመን የማይሽራቸው አድርጎ በመስራት ያስረከበን ይህ ታላቅ የኢትዮጵያ ልጅ የተገኘው ከወሊጋ ምድር ሲሆን አገራችን ካፈራቻቸው አይረሴ ድምጻውያን አንዱ ነበር። በ80ዎቹና 90ዎቹ የነበረ ትውልድም በሚገባ ያስታውሰዋል። በእርሱ ሙዚቃዎች ያልደመቁ በአላትና ሠርጎችም አልነበሩም። ታላቁ የጥበብ ሰው በሙዚቃ መንገድ ብዙ አመታትን ተጉዞ በመጨረሻም 1999 ዓ.ም የሕይወቱ ማብቂያ ነበረች።ብዙ ነገሮቹ በነበር የቀሩ የታሪክ ትዝታዎች ሆነዋል። የእርሱ ስም ገኖ ከወጣበት ዘመንና በተለያዩ ምክንያቶች የዝነኝነቱን ያህል የሕይወት ታሪኩ በአግባቡ ተጽፎ ከታላላቆች የሕይወት ባህረ መዝገብ ሳይሰደር አልፏል። ድምጻዊ ታደሰ ለሚዲያ ከበቁ ሥራዎቹ ባልተናነሰ ሁኔታ በውስጥ ለውስጥና መድረኮች ላይ የሠራቸው ሥራዎች ብዙ ናቸው። በዚህ የፋሲካ በአል አበርክቶልን የሄደውን ሙዚቃ እንደ አዲስ እያጣጣምን እርሱንም እናስታውሰዋለን።

# መጽሐፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየር የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየር የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር ገለጸ።

በትምህርት ሚኒስቴር የአይሲቲና ዲጂታል ትምህርት ዋና ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ዘላለም አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ያሉ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየርና ዲጂታላይዝ በማድረግ በስርዓተ ትምህርቱ(ካሪኩለሙ) መሰረት የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ ነዉ። እንዲሁም ከቅድመ መደበኛ እስከ 8ኛ ላሉ ክፍሎች መሰረታዊ ክህሎቶች ላይ በማተኮር የእንግሊዘኛ ቋንቋ የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል።

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ፤ ትምህርቱ የሚሰጠው እንደ መደበኛ ሳይሆን ለመደበኛ ትምህርቱ አጋዥ እንዲሆን ነው። የኦንላይን ትምህርቱ ጥሩ ይዘቶች ያሉት እና በአለምአቀፍ ደረጃ ጥሩ የሚባሉ እንደ ብሪቲሽ ካውንስል ያሉ ተሳትፈውበት የተዘጋጀና የሚተላለፍ ነው።

ለርን ኢንጊሊሽ(learn Engilish)የተሰኘው የኦንላይን ትምህርት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ በቀላሉ በእጅ ስልክ ወይም በኮምፒውተር ትምህርቱን በነጻ አውርደው መከታተል እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በገጠር አካባቢ ለሚኖሩና ኢንተርኔት ማግኘት ለማይችሉ ተማሪዎች የተቀረጹ ትምህርቶችን በሲዲ በማድረግ የሚሰጣቸው ሲሆን፤ በፕላዝማ እና ትምህርት ቤት ውስጥ ባሉ የኮምፒውተር ላብራቶሪዎች በመጠቀም



ዶክተር ዘላለም አሰፋ

ትምህርቱን መከታተል እንደሚችሉ ገልጸዋል።

የትምህርትን ጥራት ከሚጠብቁ ነገሮች ዋነኛው ትምህርትን በቴክኖሎጂ መደገፍ እንደሆነ የሚናገሩት ዶክተር ዘላለም፤ የኦንላይን ትምህርቱ የተማሪዎችን እንግሊዘኛ ቋንቋ የመናገር ፣የመስማት ፣የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ ተማሪዎች https://learnenglish.moe.gov.et የሚለውን ድረገጽ በመጎብኘት ትምህርቱን መከታተል እንደሚችሉ ተናግረዋል።

አጠቃላይ የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ የሚናገሩት ዶክተር ዘላለም፤ ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን የመጽሐፍት እጥረት ለመቅረፍም ሁሉንም የመማሪያ መጻሕፍቶቻቸውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ካዘጋጀው ዲጂታል ላይብረሪ ማግኘት እንደሚችሉም ጠቁመዋል።

ዲጂታል ላይብረሪው ብዙ ተማሪዎች እየተጠቀሙበት እንደሆነ ገልጸው፤ ሁሉም የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዲጂታል ላይብረሪውን https://elearn.moe.gov.et ብለው በመግባት በነጻ መጠቀም እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ትምህርትን በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሂደት ላይ አሁን ላይ እንደ ችግር ሊነሳ የሚችለው አብዛኛው ተማሪዎች በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በመሆኑ የኢንተርኔት ማግኘት ችግር ሊገጥማቸው መቻሉ እንዲሁም የእጅ ስልክ ወይም ታብሌት በማስፈለጉ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዘላለም፤ በየትምህርት ቤቱ አነስተኛ የኮምፒውተር ላብራቶሪ ቢኖር ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

ባንኮች፣ለትርፍ ያልተቋቋሙ የእርዳታ ድርጅቶች፣ወላጆች፣የልማት ድርጅቶች እና ነጋዴዎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት በሚችሉት አቅም ትምህርት ቤት ድረስ ወርደው ለተማሪዎች ውድ ያልሆኑ ታብሌቶችን በመግዛት እገዛ እንዲያደርጉና ትምህርትን በቴክኖሎጂ ለማገዝ የሚደረገው ጥረት አካል እንዲሆኑ ዶክተር ዘላለም ጥሪ አቅርበዋል።

# “ለውጡን ለማሻገር ምሁራን፣ ማኅበረሰቡና ፖለቲከኞች ሂደቱን ሊደግፉ ይገባል”

**- የህግ አማካሪ እና ጠበቃ ዶክተር ዳባ ጨፋ**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ ፡- በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ለውጥ እንዲሻገር ምሁራን፣ ማኅበረሰቡና ፖለቲከኞች በጎውን በጥሩነቱ በማድነቅ ሊሻሻል የሚገባውን ደግሞ ድርሻ በመውሰድ ሂደቱን በለውጥ አስተሳሰብ ሊደግፉት እንደሚገባ የህግ አማካሪ እና ጠበቃ ዶክተር ዳባ ጨፋ ገለጹ፡፡

ዶክተር ዳባ እንዳስረዱት፤ ለውጡን ማስቀጠል መንግስት ብቻውን ሊተገብረው የሚችለው አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ምሁራን እና አመራሮች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ለውጡ ተሻግሮ ለኢትዮጵያ መልካም ውጤት እንዲያመጣ በለውጥ እሳቤ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ጥሩውን ማሞገስ እና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ለውጡ የሚፈልገውን የራስን ድርሻ ወስዶ ለትግበራው መትጋት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በአይነቱ የተለያየ ችግር ያዘለ የፖለቲካ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን አስተናግዳለች፡፡ በተለይ ከአምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት በአገሪቱ ከታዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ለየት ባለ መልኩ ኅብረተሰቡን ያሳተፈ የለውጥ መነሳሳት በመላበስ በቁርጠኝነት ሲንቀሳቀስ ቆይቷልም ብለዋል፡፡

መንግስት በቁርጠኝነት ለመለወጥ ኃላፊነት የወሰደው ባለፈው የፖለቲካ አውድ ውስጥ የነበረው ችግር ባልጠራበት ሁኔታ ነው፡፡ የቀደመው ባልተቀየረበት እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው አስተሳሰብ በቀጠለበት ሂደት ውስጥ ኃላፊነቱን በመውሰድ ለውጥ አመጣለሁ በማለት ሲንቀሳቀስ መቆየቱንም ነው የተናገሩት፡፡

በሂደቱ በአንድ በኩል ባለፉት የፖለቲካ ምሕዳር ውስጥ የነበሩና ለውጡን ለመቀበል የማይፈልጉ ኃይሎች ፈተና ነበሩ፤ መንግስት ለውጡን ለማሳለጥ አዲስ አስተሳሰብ ይዞ መነሳቱ ደግሞ በሌላ ወገን መንግስትንም ሕዝብንም ዋጋ ሲያስከፍል ቆይቷል ብለዋል፡፡

የሚታዩ ለውጦች አሉ፡፡ ለውጡ ተሻግሮ እውን እንዲሆን በመንግስትም ሆነ በሕዝብ በኩል የሚቀሩ ተግባራትን ለይቶ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለውጥን ማሳለጥ የሚቻለው ጥሩውን ነገር በመደገፍ፣ መጥፎውን ደግሞ በማረም ሊሆን ሲገባ በማኅበረሰቡ የተለመደው እና እየሆነ ያለው የተለየ ነው ብለዋል፡፡

ለውጡን ወደፊት ለማራመድ የሚደረጉ በርካታ ጥረቶች ቢኖሩም ወደ ኋላ የሚጎትቱ በርካታ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች አሉ ያሉት ዶክተር ዳባ፣ ይህ ደግሞ ለውጡ በሚፈለገው መልኩ እንዳይጓዝ እንቅፋት ፈጥሯል ብለዋል፡፡

ይህንን ችግር ለመሻገር ሁሉም ዜጋ፤ በተለይ ምሁራን እና ፖለቲከኞች ግንባር ቀደም በመሆን ለውጡ ለመላው ህብረተሰብ ተጨባጭ እድገት ይዞ እንዲያመጣ የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

## ምዕመኑ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከክፋትና ጥላቻ ማራቅ አለብን ብለዋል። በትንሳኤው የተሸነፈው ክፋትና ጥላቻ በመሆኑ ሰላም በእያንዳንዳችን ልቦና ውስጥ መስፈን ያለበት ጉዳይ ነው ያሉት ፓስተር ጻድቁ፤ በዓሉን ስናከብር የተቸገሩትን በማሰብ እና በመርዳት ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል።

ትንሳኤውን ስናከብር ራሳችንን ከክፋትና ጥላቻ በማራቅ መሆን አለበት፡፡ ይህም የዕለት ተዕለት ድርጊት ሊሆን ይገባል ሲሉ ገልጸዋል። በዓሉ የደስታ፣ የመተሳሰብና የመረዳዳት እንዲሆንልን እመኛለሁ ብለዋል።

የኢትዮጵያ መካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ በበኩላቸው፤ በዓሉን ስናከብር ከወትሮው በተለየ እርስ በርስ በመተሳሰብ፣ አቅመ ደካሞችን በመርዳት፣ ጎዳና ያሉትን ዜጎች ከጎዳና በማንሳት፣ ያዘኑትን በማጽናናት እና መልካም ነገር በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በሀገሪቱ በተለያዩ ክፍሎች ያሉትን ግጭቶች በንግግርና በውይይት በመፍታት ዜጎች በሰላም እንዲኖሩ በሚደረገው ጥረት ምዕመናኑ የራሱን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ጠቁመው፤ በዓሉ ለመላ ክርስቲያኑ የፍቅር፣ የደስታ፣ የሰላምና የመተሳሰብ ይሆን ዘንድ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## “የክልል ልዩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኃይል የሚባል አደረጃጀትና መዋቅር የለም" ብለዋል። በመሆኑም የጸጥታ መዋቅሩ መከላከያ፣ ፌዴራል ፖሊስና የክልል ፖሊስ ሲሆን፤ በክልል ልዩ ኃይሎች ስም ተልዕኮም ሆነ ግዳጅ የሚቀበል ኃይል አይኖርም ሲሉ አረጋግጠዋል።

ከዚህ በኋላ በመረጡት አደረጃጀት መሰረት ሁሉንም ወደ ተመደቡበት የማጓጓዝና ወደ ስልጠና የማስገባት ስራ ይከናወናል ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# “የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መውረድን እንደሚጠይቅ፤ እውነተኛ መውደድ በቅድመ ሁኔታዎች እንደማይታጠር ክርስቶስ በተግባር አስተምሮናል ሲሉ ገልጸዋል።

የትንሣኤ በዓል የዕርቅና የይቅርታ በዓል መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤በትንሣኤው አዲስ የምሕረት ምዕራፍ ተከፍቶ የሰው ልጆች የርግማን ሰነድ ተሰረዘ እንጂ የበዳዩ በደል ተዘርዝሮ ሂሳብ ወደ ማወራረድ አልተገባም ብለዋል።

“የተበደለ ፈጣሪ ሳለ ልጁን ለመሥዋዕት የላከው እሱ ነው። ዕርቅ አውራጁም እሱ፣ ይቅር ባዩም እሱ ነው። የዕርቅ ዓላማው ሰላም በማውረድ መከራን ማጥፋት ነውና ተበዳዩ ይቅር ቢል የእሱን ታላቅነት ያሳያል እንጂ ተሸናፊ እንደማያደርገው የትንሣኤው ታሪክ ያስተምረናል ነው ያሉት።

ዛሬ በትንሣኤው በዓል ሰሞን ሆነን ባለፉት ረጅም ዘመናት በሀገራችን የተፈጠሩ ጸብና አለመግባባቶችን በዕርቅ ስለመቋጨት ማሰብና መወሰን አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ፤ በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ የትናንት መቆራቆሶች የነገ ተስፋችንን እንዳያጨልሙ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መክረንና ዘክረን እንቋጫቸው። ከሂሳብ ማወራረድ አባዜ እንውጣ፤ የሐሳብ ልዩነቶች ከጠረጴዛ አልፈው የዐውደ ውጊያ መነሻ እንዳይሆኑ ለስሜቶቻችን ልጓም እናበጅላቸው፤ እልህና ክፋት ውድቀትን፣ ቅንነትና ምክክር ዕድገትን እንደሚያመጣ እንወቅ ሲሉ አስገዝበዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ሀገራችን የትንሣኤዋ ዋዜማ ላይ ነች። የምናያቸው ፈተናዎች የሕማማት ሰሞን ፈተናዎች ናቸው። እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ሁሉ የሀገራችን ብልጽግና እውን እንደሚሆንና የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ ምንም ጥርጥር የለውም። ይኽ የሚሆነው ግን እንደ ኒቆዲሞስ ተስፋን ሰንቀው ወደ ትንሣኤው ብርሃን የሚገሠግሡ፣ እንደ ዮሐንስ ውኆንብሩን ሁሉ በጽናት የሚያልፉ፣ እንደ ሮማዊው መቶ አለቃ እውነትን በድፍረት የሚመሰክሩ ዜጎች ሲበዙ ነው።

የትንሣኤው ጸጋ የግቡን ምንነት እንጂ ሂደቱን እንደማይጠቁም ሁሉ፤ “የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን ከመሆን አይቀርም” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ይህን የምንለው ጉዞው ቀላል እንደማይሆን በማመን ነው። በተለይ እንደ ይሁዳ ሀገርን በሽርፍራፊ ሳንቲም ለመሸጥ የማያመነቱ ሰዎችን ይዘን ጉዟችን ቀላል አይሆንም ብለዋል፡፡

ዜጎቻችን ቀናውን መንገድ የሚጠቁሙትን ትተው፣ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ላሉ፣ ቅንነት በጎደለው ዕውቀት ለተሞሉ ሰዎች ሙሉ ጊዜያቸውን መስጠት ከጀመሩ ሩጫችን ወደ ርምጃ መለወጡ እንደማይቀር የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በብልጽግና ጉዟችን ውስጥ ከፈተናችን በላይ መሆን እንድንችል የፈተናችንን ዓይነትና ፈታኞቻችንን ለይተን ማወቅ እና በጽናት ለመታገል መወሰን አለብን ነው ያሉት።

ወደ ተራራ መውጣት ቁልቁለት እንደ መውረድ አይቀልም፤ ላብና ትንፋሽ ይጠይቃል። ወደ ትክክለኛ መዳረሻ የሚወስድን ትክክለኛ መንገድ መርጦ መጓዝን ይሻል፤ ከምንም በላይ በየምዕራፉ የሚገጥሙ እሾህና ጋሬጣዎችን፣ ቋጥኝና አውሬዎችን በሰላም ለመሻገር መተባበርና መደጋገፍ ከተጓዦች ይጠበቃል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የብልጽግና ጉዞ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት የኅብረት ጉዞ እንጂ ጥቂቶች የሚያሸንፉበት የጥሎ ማለፍ ሩጫ አይደለም። ትንሣኤው አይቀሬ ነው። ፈተናው ተሸናፊ ነው። የጸናም አሸናፊ ይሆናል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ዓለም አቀፍ



## አነጋጋሪዎቹን ምስጢራዊ ሰነዶች "አሾልኳል' ተብሎ የተጠረጠረው አሜሪካዊ የአየር ኃይል አባል ክስ ተመሠረተበት

ምስጢራዊ የመረጃ እና የመከላከያ ሰነዶችን አሾልኮ አውጥቷል ተብሎ የተጠረጠረው አሜሪካዊው የአየር ኃይል አባል ክስ ተመሰረተበት። የ21 ዓመቱ ጃክ ቴሼራ ቦስተን በሚገኘው ፍርድ ቤት አርብ ሚያዝያ 5 ቀን2015 ዓ.ም ሲቀርብ እጆቹ በካቴና ታስሮ እና የማረሚያ ቤት የመለያ ልብስ ለብሶ ነበር። በዕለቱ ችሎት ላይም በፍርድ ቤቱ ውስጥ «እወድሃለሁ ጃክ» የሚል ድምጽ የተሰማ ሲሆን፣ ተከሳሹም «እኔም እወድሃለሁ አባቴ» የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

ጃክ ቴሼራ ምስጢራዊ እና ያልተፈቀደለትን የመከላከያ መረጃን በማውጣት ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን፣ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ እስከ 15 ዓመት የሚዘልቅ እስር ይጠብቀዋል። በተጨማሪም ምስጢራዊ ሰነዶች እና መረጃዎችንም ሕጉ ሳይፈቅድለት በመያዝ ክስም ይጠብቀዋል።

ሰነዶችን አሾልኮ በማውጣት ክስ እስከ 10 ዓመት የሚቆይ እስር እንዲሁም ያልተፈቀደለትን መረጃዎችን በመያዝ ደግሞ አምስት ዓመት በድምሩ የ15 ዓመት እስር እንደሚጠብቀው ነው የተገለጸው። ከሰሞኑ ከፔንታገን በደርዘን የሚቆጠሩ ሾልከው የወጡ ሰነዶች የዩክሬንን ጦርነትን አስመልክቶ አሜሪካ ያላት ግምገማ እንዲሁም አሜሪካ ከአጋሮቿ ጋር ያላትን ግንኙነት እና የምታደርጋቸውን ስለላዎች ይፋ አድርገዋል።

እነዚህ ያፈተለኩ መረጃዎች አሜሪካንን ያሳፈሩ ሲሆን፣ በአገሪቱ ምስጢራዊ መረጃዎች አጠባበቅ እና ደኅንነት ላይም ጥያቄዎችን አስነስተዋል። ጃክ ቴሼራ ሐሙስ ዕለት ማሳቹሴትስ በሚገኘው የወላጆቹ ቤት እያለ ነበር በታጠቁ የአሜሪካ የፌዴራል ምርመራ ቢሮ (ኤፍቢአይ) ወኪሎች በቁጥጥር ስር የዋለው።

ጃክ ቴሼራ በአሁኑ ወቅት በእስር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፣ የሕግ አስከባሪ አካላት ፈጣን እርምጃ በመውሰድ መረጃዎቹን በሚያሾልከው ምንጭ ላይ ለመድረስ ያደረጉትን ምርመራ አድንቀዋል። ፕሬዚዳንቱ አክለውም ለወደፊቱም ምስጢራዊ መረጃዎችን ለመጠበቅ እና እንዳይወጡ ለማድረግ የአሜሪካ ጦር እና የስለላ ድርጅት ጥብቅ መመሪያ ማስተላለፉን ተናግረዋል።

ሾልኮ የወጣው መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ዲስኮርድ በተሰኘው መልዕክት መላላኪያ መተግበሪያ ሲሆን፣ ይህንንም ጃክ በበላይነት ይቆጣጠር ነበር ተብሏል። የዲስኮርድ አባላት አብዛኛውን ጊዜ ስለ ጂኦ ፖለቲካዊ ጉዳዮች እና ጦርነቶች ይወያያሉ። የኤፍቢአይ ልዩ ወኪል ፓትሪክ ሉኬንሆፍ ለፍርድ ቤቱ በሰጡት ምስክርነት ተጠርጣሪው እነዚህን ምስጢራዊ ሰነዶች በታኅሣሥ ወር መለጠፍ እንደጀመረ ተናግረዋል።

የመጀመሪያዎቹ መረጃዎች ጽሑፎች የነበሩ ሲሆን፣ በኋላ ግን ፎቶግራፎችንም ማውጣት እና መለጠፍ መጀመሩን ተናግረዋል። የፔንታገን ባለሥልጣናት ስለ ጉዳዩ የተረዱትም ከዚህ መተግበሪያ ውጪ መረጃዎቹ በመለጠፋቸው ነበር። ጃክ የማሳቹሴትስ የአየር ኃይል ብሔራዊ ዘብ የደኅንነት ክንፍ ባልደረባ ሲሆን፣ የሥራ ድርሻውም የአሜሪካ አየር ኃይል ዓለም አቀፍ ኮሚዩኒኬሽን እንደነበረ የዘገባው ቢቢሲ ነው።

## የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ የጭስ ቦምብ ጥቃት ተሰነዘረባቸው



የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ በአንድ ሕዝባዊ ዝግጅት ላይ እያሉ የጭስ ቦምብ ተወረወረባቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸውም ከአካባቢው ማስወጣት እንደቻለም ተዘግቧል። ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ዋካያማ በተባለ ስፍራ ንግግር እያደረጉ በነበረበት ወቅት የጭስ ቦምብ ወርውሯባቸዋል ተብሎ የተጠረጠረ ግለሰብ በቁጥጥር ስር መዋሉን የጃፓን መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

በስፍራው ላይ የነበሩ የዐይን እማኝ አንድ ሰው የሆነ ነገር ሲወረውርና ጭስ ሲወጣ ማየታቸውን የተናገሩ ሲሆን፣ ሌላ የዐይን እማኝ ደግሞ ፍንዳታ እንደሰሙ ተናግረዋል። ነገር ግን በጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት አልደረሰም ተብሏል። ፖሊሶች የጭስ ቦምቡን ወርውሯል ተብሎ በታመነው አንድ ግለሰብ ላይ ሲረባረቡ የሚያሳይ ቪዲዮም ወጥቷል።

ተጠርጣሪ የተባለው ግለሰብ በቁጥጥር ስር መዋሉን ፖሊስ ቢያስታውቅም ተጨማሪ ማብራሪያ ግን አልተሰጠም። ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ በስፍራው ከፍተኛ ፍንዳታ እንደነበር መናገራቸውን የጃፓን መንግሥታዊ ሚዲያ ኤንኤችኬ ዘግቧል።

«ፖሊስ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምርመራ እያደረገ ነው። ነገር ግን በዚህ አጋጣሚ በርካታ ሰዎችንስላስጨነቅኩ ይቅርታ መጠየቅ እፈልጋለሁ» ማለታቸውም ተዘግቧል። ኤንኤችኬ በርካታ ሰዎች ከስፍራው ሲሸሹ እንዲሁም ተጠርጣሪው ግለሰብ በፖሊስ ሲወሰድ የሚያሳይ ቪዲዮም አሰራጭቷል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዋካያማ የሚገኘውን የዓሣ ማጥመጃ ስፍራን ጎብኝተው የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ንግግራቸውን በጀመሩበት ወቅት ነው የጭስ ቦምቡ የተወረወረባቸው። ፉሚዮ ቦምቡ ሳይነካቸው ማምለጥ መቻላቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በጃፓን ውስጥ እንዲህ ዓይነት ጥቃቶች የተለመዱ ባይሆንም፤ ነገር ግን ባለፈው ዓመት በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ላይ እያሉ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሺንዞ አቤ፣ በአደባባይ በጥይት ከተገደሉ በኋላ በፖለቲከኞች ደኅንነት ዙሪያ ስጋት ነግሷል።

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት
Ethiopian Intellectual Property Office

## ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

### የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!

የዓለም አእምሯዊ ንብረት ቀን በየዓመቱ ሚያዝያ 18 የአእምሯዊ ንብረት ግንዛቤን በሚያሳድጉ ሁነቶችና የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት በሚሰይመው መሪ ቃል በመላው ዓለም ይከበራል።

«አእምሯዊ ንብረትና ሴቶች፣ ኢኖቬሽንና ፈጠራን ማፋጠን / Women and IP: Accelerating innovation and creativity» የሚል መሪ ሃሳብ ያነገበውን የዘንድሮ አእምሯዊ ንብረት ቀን በሀገራችን በፓናል ውይይትና የፈጠራ ሥራዎች ዓውደ-ርዕይ ሚያዝያ 18 እና 19 በሳይንስ ሙዚየም ይከበራል።

ሴቶች ፈጠራን በማመንጨት፣ አእምሯዊ ንብረትን ጥቅም ላይ በማዋል፣ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር፣ የማህበረሰቡን ችግር በመፍታትና ሌሎችንም ፋይዳዎች በማበርከት ዓለማችን አሁን ላለችበት የዕድገት ደረጃ ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ሀገራችንም በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ ኪነ-ጥበብና ሌሎችም ዘርፎች ብዙ ውጤታማ እንስቶችን አፍርታለች። ሴቶች ያላቸውን እምቅ አቅምና ተሰጥኦ አጉልቶ ለማሳየትና የሚገጥማቸውን ተግዳሮቶች ለማቃለል የትብብር ሥራዎች አስፈላጊነታቸው እሙን ነው።

አእምሯዊ ንብረት የሰው ልጅ አእምሮውን ተጠቅሞ የሚያመነጨውን የፈጠራ ሥራዎች ለማስጠበቅና የፈጠራ ባለሙያዎች ከመብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የጥበቃ ሥርዓት ሲሆን ፓተንት፣ ንግድ ምልክት፣ ቅጅና ተዛማጅ መብቶችና ሌሎችም ዘርፎችን ያካትታል።

በዚህ ዓለም አቀፋዊ ሁነት የፈጠራ ሥራዎች ዓውደ-ርዕይ መርሃ- ግብር የሴቶችና ወጣቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ፣ የጥናትና ምርምር፣ የሥራ ፈጠራ ተቋማትና ሌሎችም የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ለእይታ ያቀርባሉ።


**ሚያዝያ 18 እና 19 በሳይንስ ሙዚየም በመገኘት ዓውደ-ርዕዩን እንዲጎበኙ ተጋብዘዋል!!!**



## መልካም የትንሳኤ በዓል ይሁንልዎ !

## የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

# ስፖርት



## የአካል ጉዳት ያልበገረው የስፖርቱ ዓለም ጀግና

**ብርሃን ፈይሳ**

በየትኛውም ወቅትና ሁኔታ ጀግና ይፈጠራል። በጦር አውድማ የተዋደቀውም፣ ለመልካም ተግባር የተጋውም፣ ለሰው ልጆች ወይም ለሌሎች ፍጥረታት ሲል ዋጋ የከፈለውም፣ በስፖርት መድረክ አገሩን ያስጠራም በየመስኩ ጀግና ነው። የአንዳንድ ጀግኖች ገድል ግን ለየት ያለና ሁሌም የሚታወስ ይሆናል። ከእንዲህ ዓይነት አይረሴ ጀግኖች መካከል ከስፖርት የታሪክ ማህደር ውስጥ አንዱን እንመልከት።

ሙሉ ስሙ ቴራንስ ስታንሊ ፎክስ ይባላል። በተለየ የሚታወቀው ቴሪ ፎክስ በሚል አጭር መጠሪያው ነው። ይህ ሰው ካናዳዊ ነው፤ በ1958 ይህቺን ዓለም ሲቀላቀል ቤተሰቦቹ ከሌሎች ሰዎች የተለየ ባህሪ እንዳለው ገና በሕፃንነቱ ነበር የተረዱት። እጅግ የበዛ የተወዳዳሪነት (የተፎካካሪነት) ስሜት ሲኖረው፤ መሸነፍ ደግሞ ሞቱ ነው። ስኬት ፊቱን እስኪያበራለት ከመታገል ወደኋላ የማይለው ፎክስ በቅድሚያ የተቀላቀለው በትምህርት ቤቱ የሚገኝ የቅርጫት ኳስ ስፖርት ቡድንን ነበር። ትክለሰውነቱን የተመለከቱት አሰልጣኝ ደግሞ አትሌቲክስን እንዲሞክር ምክረሃሳብ ሰጡት። በመጀመሪያ አሰልጣኙን ለማስደሰት ሲል እንደተባለው ሩጫን ቢጀምርም የኋላ ኋላ እጅግ ስለወደደው ሁለቱን ስፖርቶች ጎን ለጎን ማስኬድ ጀመረ። የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን ሲያጠቃልልም የዓመቱ ምርጥ አትሌት ተብሎ ለሽልማት በቅቶ ነበር።

ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመግባትም ከስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍሎች አንዱን ካጠና በኋላ የስፖርት መምህር ሆነ። ስፖርትን የሕይወቱ አካል ያደረገው ፎክስ ከመምህርነት ሥራው ጎን ለጎን በአገሩ የሚገኙ ቅርጫት ኳስ ቡድንን በመቀላቀል በውድድሮች ላይ ይካፈል ነበር። እአአ በ1976 ግን ቀድሞ በደረሰበት የመኪና አደጋ ምክንያት ችላ ያለው የጉልበቱ ጉዳት ማገርሸት መጀመሩን ተከትሎ የሕይወቱ መስመር ተቀየረ። እየባሰ በሄደው ህመሙ ምክንያት ሃኪም ቤት የተገኘው ፎክስ፤ ህመሙ ወደ ካንሰርነት እየተለወጠ በመሆኑ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲባል እግሩ መቆረጥ እንዳለበት ተነገረው። ብርቱው ወጣት ከከባዱ ህመም አገግሞ በሰው ሰራሽ እግር ወደ ቀደመ ሕይወቱ ለመመለስ ጥቂት ወራት ብቻ ነበር የፈጀበት።

ፎክስ የአካል ጉዳቱን ተከትሎ ከካናዳ ዊልቸር ስፖርቶች ማህበር ጋር በቅርበት መስራት ሲጀምር፤ ከዊልቸር ቅርጫት ኳስ ስፖርት ቡድን ደግሞ እንዲቀላቀላቸው ጥሪ ቀረበለት። ፈጣኑ ፎክስ ስለ ስፖርቱ ተገንዝቦ ተወዳዳሪ ለመሆን የፈጀበት ከሁለት ወር ያነሰ ጊዜ ብቻ ነበር። ከቡድኑ ጋር በካናዳ በሚካሄዱ ቻምፒዮናዎች ላይ በመካፈልም ሶስት ጊዜ አሸናፊ መሆን ሲችል፤ በሰሜን አሜሪካ ቅርጫት ኳስ ማህበርም እአአ በ1980 ምርጥ ተጫዋች በሚል ሊሰየም ችሏል። በልጅነት የተጀመረው የስፖርት ሕይወቱ በአካል ጉዳት የቀጠለ ይሁን እንጂ፤ የዘወትር ህልሙ ማራቶንን መሮጥ ነበር። በእርግጥ ነገሩ የማይሆን ይምሰል እንጂ፤ ማነሳሻ የሆነው ግን እሱን በመሰለ የአካል ጉዳት ማራቶንን ሮጦ ያጠናቀቀ ሰው ታሪክ ነበር።

ይህን ሃሳብ ቤተሰቡን ጨምሮ በርካቶች ቢቃወሙትም ለ14 ወራት ዝግጅት ካደረገ በኋላ፤ ዓላማው ከሩጫ ባለፈ የገቢ ማሰባሰቢያ እንደሚሆንና ይኸውም ለካንሰር ህክምና እና ምርምር እንደሚውል አሳወቀ። ‹‹የተስፋ ማራቶን›› ሲል የሰየመው ይህ የግሉ ሩጫም ከገቢ ማሰባሰቡ ጎን ለጎን ስለ ካንሰር ግንዛቤ የማስጨበጥ ዓላማንም ያነገበ ነበር። ሩጫው በአንድ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ እግር በመሆኑ እጅግ ፈታኝ መሆኑ አያጠራጥርም። ነገር ግን ጽናት መለያው የሆነው ፎክስ በቅድሚያ 1 ሚሊዮን ዶላር ቀጥሎ 10 ሚሊዮን ዶላር ማሰባሰብ ቻለ። ይህ ዓላማው በመላው ካናዳውያን ዘንድ እውቅና በማግኘቱም በትልልቅ ውድድሮች ላይ እስከመጋበዝ ደረሰ፤ በመላው ዓለምም ለበርካቶች ተምሳሌት ሆኗል። በገቢ ማሰባሰቢያውም ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ አግኝቷል።

በመጨረሻ ግን የካንሰር ህመሙ ተቀስቅሶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ በሃኪሞች አስገዳጅነት ሩጫውን አቁሞ ህክምናውን ጀመረ። አስከፊ ከሆነው የወራት የካንሰር ትግል በኋላ ግን ተሸነፈ፤ እአአ በ1981 ሕይወቱ አለፈ። ይህንን ተከትሎም በአገሩ ብሔራዊ ጀግና ተሰኘ። እሱን የሚያስታውሱ ሐውልቶች ቆሙለት፣ መንገዶችም በስሙ ተሰየሙለት። የእሱ የሕይወት ታሪክ ላይ የሚያጠነጥኑ ፊልሞችም የተሠሩ ሲሆን፤ ቤተሰቦቹም በርካታ ሽልማቶችን ከህልፈቱ በኋላ ተበርክቶላቸዋል።




ቴሪ ፎክስ፣




## የትንሳኤ በዓልና አከባበር

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? መቼም «ቆንጆ ነው!!!» እንደምትሉኝ አልጠራጠርም። ምክንያቱም በሚገባ እያነበባችሁና እየተፈተናችሁ በጥሩ ውጤት ላይ ስለምትገኙ። ይህ ደግሞ የአንድ ጎበዝ ተማሪ ባህሪ ነው። ለማንኛውም ልጆች ዛሬ ቀኑ በዓል ነውና ስለዚህ በዓል ምንነትና በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እንዴት እንደሚከበር እነግራችኋለሁ።

«ትንሳኤ» የሚለው ቃል ከግዕዝ ቋንቋ የተገኘ ነው። መገኛ ቃሉም «ተንሥአ» ተነሣ የሚለው ግሥ ይሆናል። ስለሆነም ትንሳኤ ማለት መነሣት፣ አነሣሥ፣ ሐዲስ ሕይወት ማግኘት ማለትን ያመለክታል። ልጆች የትንሣኤ በዓል በቃሉ ምስጢርም ሆነ በይዘቱ ስለሚመሳሰል በሌላ አጠራር «ፋሲካ» ይባላል። «ደግሞ ፋሲካ ማለትስ?» የሚል ጥያቄ እንደምታነሱ አስባለሁ። ስለዚህም ፋሲካ ማለት በእብራይስጥ ቋንቋ «ፌሳሕ» በጽርእ፤ በግሪክኛው ደግሞ «ስኻ» ይባላል።

ወደ ግዕዝና አማርኛ ቋንቋችን ስንመልሰው ደግሞ ማዕዶት፣ የቂጣ በዓል፣ እየተቸኮለ የሚበላ፣ መሥዋዕት መሻገር፣ መሸጋገር ማለት ነው። ፈረንጆቹ በእንግሊዝኛው «ስአቨር» ይሉታል። ታሪካዊ መልዕክቱም በዘመነ ኦሪት ይከበር የነበረው በዓለ ፋሲካ እስራኤል ዘሥጋ ከግብጽ የባርነት ቀንበር ወደ ነፃነት የተላለፉበት፣ ከከባድ ሐዘን ወደ ፍጹም ደስታ የተሸጋገረበት በዓል ነበር። በዚህም ኦሪታዊ ምሳሌ የነበረው በዓል አሁን ወደ አማናዊው በዓል ተቀይሮ «ትንሳኤ» ወይም «ፋሲካ» ተብሎ ይከበራል።

ልጆች ስለ ምንነቱ ይህንን ያህል ካልኳችሁ «እኛ ኢትዮጵያውያን በዓሉን እንዴት እያከበርነው እንገኛለን?» ወደ’ሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ልግባ።

ልጆች፣ ትንሳኤን ብዙዎቻችሁ ደስ ብሏችሁ እንደምታከብሩት ይሰማኛል። ምክንያቱም ይህ በዓል ሃይማኖታዊም ባህላዊም ሥርዓት ስለሆነ ማለት ነው። ሃይማኖታዊ በዓሉ የክርስቶስን ለሰው ልጅ ሲል መሰቀሉን እናይበታለን። የሰው ልጅ ፍቅር ስቦት ለሞት፣ አብቅቶት፣ በሞቱ ሞትን ድል ነስቶ ትንሳኤን እንዳሳየንም እናስብበታለን። እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ፤ ለሰው እስከሞት ድረስ የታመንን እንድንሆንም የተማርንበት ስለሆነ በደስታ እናከብረዋለን።

ወደ ባህላዊ ክዋኔው ስንገባ ደግሞ ብዙ ነገሮችን የምናስተውልበት በዓል ነው። አንዱ ልጆች ከትምህርት ቤት ጥቂት ቀናትን አርፈው ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ዘመድ አዝማድን እንዲጠይቁ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። ይህ ቀን የደስታና የፍስሀ ጊዜ ነውና ሰዎች ተሰባስበው ፍቅርን የሚቀባበሉበት ዕለትም ነው፤ ከቤተሰብ ጋር ሰፊ ጊዜ የምናሳልፈበት ቀን።

መብላት፣ መጠጣቱ፤ መታረቅና በፍቅር መገናኘቱ የሚጠብቅበት ዕለትም ነው። ልጆች ከተማ ያለው ገጠር የሚሄድበት አጋጣሚም የሚያገኘው በዚሁ በፋሲካ ጊዜ ነው። ምክንያቱም በባህሉ ዘንድ «አክፋይ» የሚባል ነገር አለና ያንን ይዞ ዘመድ አዝማድን መጠየቅ ግድ ነው።

አክፋይ ማለት ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ በዓለ ሃምሳ ድረስ ሰው በየቤተዘመዱ የሚያበረክተው ስጦታ ነው። ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ደስታውን ለመግለጽ አንዱ ወደ አንዱ ወዳጁ የተለየ ስጦታ ይዞ ይሄዳል። ለምሳሌ ዳቦ፤ ሙክት በዋናነት ከሚወሰዱ ገጸበረከቶች መካከል ናቸው። አንድ ሰው ይህንን ካደረገ አጸፋውንም ይጠብቃል።

ልጆች በአክፋይ ወዳጅ ዘመድ ጋር የሚደረግ ስጦታ ብቻ አይደለም የሚከናወነው። ድሆችም ይጠየቃሉ። በጣም አስደሳችና ተስማሚ የሚሆነውም ይህ ሲደረግ ነው ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም የማህበራዊ ኑሮም ስሜትም መገለጫ ነውና በአክፋይ ስጦታ የማይደሰት አካል አይኖርም። ምክንያቱም ተግባሩ በሕዝቡ ዘንድ ያለውን መተሳሰብ፤ መረዳዳት ያሳያል። የፍቅሩን ዋጋም ያስረዳል። ስለዚህም በክርስትና አማኞች ዘንድ አክፋይ ይዞ «እንኳን አደረሳችሁ»፣ «እንኳን አደረሰን» የሚባባልበት ቀን ሆኖ ያልፋል።

ልጆች፣ ሌላው የፋሲካ ገጸበረከት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በኢትዮጵያ ሥርግ እጅግ ከሚዘወተርባቸው ወሮች መካከል አንዱ (ሚያዝያ) ስለሆነ ብዙ ሰዎች ትዳር ይመሰርቱበታል፤ ጎጆ ይቀልሱበታል። ምክንያቱ ደግሞ በክርስትናው ዘንድ ሃምሳ ቀን ሙሉ የሚበላበት ወቅት መሆኑ ነው። አርብ፣ ረቡዕ ጭምር አይጾምም። ስለዚህም ሁሉም ደስታውን ለማራዘም ሲል ጊዜውን ይጠቀምበታል። እናም ልጆች ይህንን ጊዜ ተጠቅመው በስፋት ለሚጨፍሩበትና ለሚጫወቱበት የመዝናኛ ጊዜያቸው ይሆንላቸዋል።

ልጆች «ለመሆኑ በዓለም ዙሪያ የሚገኙትስ እንዴት ይህንን ጊዜ ያሳልፉታል?» ካላችሁ እንደ ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ነው። የእነርሱ የአከባበር ሥርዓትና የቀናት ልዩነት ይኖረዋል እንጂ በስፋት በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ልዩ ትኩረትን ሰጥቶት ነው ሁሉም የሚያከብረው ነው። ክርስቲያኖች በጣም አስፈላጊ ወቅትና ጊዜ አድርገው ይወስዱታልም። ምክንያቱም ለልጆች አስደሳች እና አዝናኝ ነገርን የሚያሳውቁበት ዕለት ቢኖር ትንሳኤ ነውና።

ልጆች ከትንሳኤ በኋላ ባሉት ጊዜያት ሰዎች በተለይም በዓሉን የሚያከብሩት አካላት ምን ዓይነት ሰላምታ እንደሚለዋወጡ ታውቃላችሁ? መቼም ብዙዎቻችሁ «እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው በሰላም አደረሳችሁ!!!» ነዋ እንደምትሉኝ አልጠራጠርም። ይህም ይባላል፤ ልክ ናችሁ። ከዚህ ይልቅ ግን በዓሉን የሚገልጽ አንድ ሰላምታ አለ። ይህም በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ምልልስ ያለበት ሰላምታ ነው።

‹‹ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን›› ሲል አንዱ ሌላኛው ተቀባይ ደግሞ ‹‹በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን›› ይላል። ይቀጥልና ሌላኛው ‹‹አሰርዎ ለሰይጣን›› ሲል መላሹ ደግሞ ‹‹አግዓዝዎ ለአዳም›› የሚል ምላሽ ይሰጣል። ‹‹ሰላም›› ሲል መላሹ ‹‹ሰላም›› ይላል። ‹‹እምይእዜሰ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም›› በማለት ሰላምታው ይጠናቀቃል።

ትርጉሙ ምን መሰላችሁ «ክርስቶስ ከሙታን በታላቅ ኃይልና ስልጣን ተነሳ፤ ሰይጣንን አስሮ አዳምን ነጻ አወጣው። በምድር ላይ ሰላምም ሆነ» ማለት ነው። ስለዚህም፣ ለዛሬ በዚህ ሰላምታ እንሰነባበት። መልካም በዓል!!!

